**የአዲስ አበባ ራስ ገዝነት እንዴት?**

**አመሃ ዳኘው**



**አዲስ አበቤ ከባልደራስ ምን ይጠብቅ?**

**(ኢንጂነየር ቢኒያም መልሳቸው)**



# ባልደራስ

1ኛ ዓመት ቁጥር 11 ቅዳሜ ሰኔ 5 ቀን 2013 ዓ.ም.

# ምርጫ የሌለው ምርጫ




## የባልደራሱ ቢንያም ታደሰ በፖሊስ ታሰረ



ባልደራስ ለእውነተኛ ዴሞክራሲ ፓርቲ (ባልደራስ) በሚያደርጋቸው የጎዳና ላይ የምርጫ ቅስቀሳ እንቅስቃሴዎች በጉልህ ተሳትፎው ከፊት ሆኖ የሚታወቀው ወጣት ቢንያም ታደሰ (ቢኒ ጊዮርጊስ) ባለፈው ሀሙስ ሰኔ 3 ቀን 2013 ዓ.ም. በፖሊስ ታስሯል። መኖሪያ ቤቱ ውስጥ በነበረበት በቁጥጥር ስር መዋሉን ዝግጅት ክፍላችን አረጋግጧል። ባልደራስ ጋዜጣ ወደ ማተሚያ ቤት እስከገባበት ጊዜ ድረስ ወጣቱ በአዲስ አበባ፤ ፒያሳ፤ ጣይቱ ፖሊስ ጣቢያ ውስጥ ታስሮ ይገኛል። ለወጣቱ መታሰር ምክንያት የሆነው በዕለቱ በመቀል አደባባይ ሊደረግ ታስቦ በፖሊስ የተከለከለው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን መንፈሳዊ አውደ ምህረት ላይ መገኘቱ እንደሆ ምንጮች ገልፀዋል። ሆኖም በዚሁ ምክንያት እየታደኑ የታሰሩት ሁሉ በነፃ ሲሰናበቱ እርሱ ብቻ ቀርቷል። ቢንያም በከተማዋ ወጣቶችን በማስተባበርና በጎ ተግባራትን በመፈፀም ይታወቃል።

## ርዕሰ አንቀፅ

# የዕጩዎች ያለመከሰስ መብት ይከበር !

በግፍ እስር ላይ የሚገኙት የባልደራስ ለእውነተኛ ዴሞክራሲ ፓርቲ (ባልደራስ) አመራሮች እስክንድር ነጋ፣ ስንታየሁ ቸኮል፣ አስቴር ስዩም እና አስካለ ደምሌ በአብይ አሕመድ አገዛዝ ታስረው የሚገኙ ቢሆንም በሕግ አግባብ ተጠርጣሪዎች እንጂ ወንጀለኞች ባለመሆናቸው የመምረጥና የመመረጥ የዜግነት መብታቸው እንዲከበር  ፍርድ ቤት ወስኗል። በመሆኑም የፊታችን ሰኔ 14 ቀን 2013 ዓ.ም. በሚደረገው ምርጫ አቶ እስክንድር ነጋ፣ አቶ ስንታየሁ ቸኮል እና ወ/ሪት አስካለ ደምሌ ለአዲስ አበባ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲሁም ወ/ሮ ቀለብ ስዩም (አስቴር) ለፌዴራሉ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሕግ የተመዘገቡ ዕጩ ተመራጮች ናቸው። ስለዚህ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የጸረ ሽብርና የሕገ መንግሥት ጉዳዮች ወንጀል ችሎት እነኝህ የባልደራስ እጩዎች እጅ ከፈንጅ በወንጀል ያልተያዙና የፖለቲካ እረኞች መሆናቸውን ብሎም ለ11 ወራት በቀጠለው ዶሴ አንዳች ጥፋት ያልተገኘባቸው መሆኑን አገናዝቦ ያለአንዳች ቅድመ ሁኔታ በነፃ እንዲያሰናብታቸው፤ ይህንን ማድረግ ካልቻለ እንኳን ጉዳያቸውን ከወህኒ ቤት ውጭ ሆነው እንዲከታተሉ በዋስ እንዲለቃቸው ዝግጅት ክፍላችን ይጠይቃል።

በአስቸኳይ ይህ የማይሆን ከሆነ ግን በየደረጃው ያላችሁ የፓርቲው አመራሮች፣ አባላት እና ደጋፊዎች ብሎም ሰፊው የአዲስ አበባ ሕዝብ ሰላማዊ የተቃውሞ ሰልፍን ጨምሮ የሕዝባዊ እምቢተኝነት ማዕበል እንድትከፍቱ እንጠይቃለን። በአምባገነኖች አገር ነፃነት በነፃ እንደማይገኝ አውቆ አዲስ አበቤና መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የነፃነት ታጋዮቹን ለማስፈታት ከወትሮው በበለጠ ተጠናክሮ መቀጠል ይጠበቅበታል።

በተለይም ከቅርብ ቀናት ወዲህ በሚኖሩበት ወህኒ ቤት በነፃነት ታጋዮች ላይ እየደረሰ ያለው አካላዊና ስነ ልቦናዊ ጉዳት በአስቸኳይ እንዲቆም የባልደራስ ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ያስጠነቅቃል። ድርጊቱ ኢትዮጵያን ወደ ባሰ ቀውስና ብጥብጥ የሚከት መሆኑን ተገንዝቦ የአብይ አሕመድ ቡድን ከእኩይ ድርጊቱና የህፃናት ብሽሽቅ ሊቆጠብ ይገባል።

ይህ ቡድን የፖለቲካ እስረኞች እነ እስክንድር ነጋ ለሚደርስባቸው ማንኛውም አይነት ጉዳት የሕግ፣ የታሪክ፣ የሞራልና የፖለቲካ ተጠያቂነት ያለበት መሆኑን መዘንጋት የለበትም። ከመሪው አብይ አሕመድ ጀምሮ እስከ መጭዎቹ ትውልደ ዘሮቻቸው ድረስ ከተጠያቂነት ሊያመልጡ አይችሉም።

የዕጩዎች ያለ መከሰስ መብት ይከበር! የፖለቲካ እስረኞች ደህንነት ይጠበቅ!

**የምርጫ ምልክት**



**ባልደራስን ይምረጡ!**


**ባልደራስ ጋዜጣ**
መስከረም 1 ቀን 2013 ዓ.ም ተመሰረተ
በየ 15 ቀኑ የሚታተም

**አሳታሚ**
**ባልደራስ**
**ለእውነተኛ ዲሞክራሲ ፓርቲ**
አድራሻ፡-6 ኪሎ ፤ ምስካየኅዙናን
መድኃኔዓለም ቤ/ክ አጠገብ

**የዝግጅት ክፍል ሓላፊ**
በቃሉ አጥናፉ ታዬ (ዶ/ር)
**ምክትል ሓላፊ**
ይድነቃቸው ከበደ
**ዋና አዘጋጅ**
ጌጥዬ ያለው
ክፍለ ከተማ፡-ቂርቆስ
ወረዳ፡- 02 የቤት ቁጥር፡-አዲስ
ስልክ፡-+2519 24 51 70 77
ኢ-ሜይል፡-newsgett@gmail.com
**ከፍተኛ አዘጋጅ**
ወግደረስ ጤናው

**አርታዒ**
መሰበወርቅ ቅጣው
ነብዩ ውብሸት
**ድረ ገጽ**
ኢሳያስ ጥጉ
**ሌይአውት ዲዛይን**
ሀብታሙ ተሾመ
+251 910 44 98 38
**ጸሐፊ**
ሕይወት ዳዊት
ፍቅሬ ታደሰ
Info@balderasfordemocracy.com

ዜና

# ሴት የባልደራስ አመራሮች የጎዳና ላይ የምርጫ ቅስቀሳ አካሄዱ

## በመሰበወርቅ ቅጣው

የባልደራስ ለእውነተኛ ዴሞክራሲ ፓርቲ (ባልደራስ) ሴት አመራሮች፣ አባላትና ደጋፊዎች ባለፈው ቅዳሜ ግንቦት 28 ቀን 2013 ዓ.ም. በአዲስ አበባ የተለያዩ አካባቢዎች በመዘዋወር የጎዳ ላይ የምርጫ ቅስቀሳ አካሂደዋል፡፡ በዕለቱ በአዲስ አበባ የተለያዩ ሥፍራዎች በተደረጉ የተሽከርካሪ እና የእግር እንቅስቃሴዎች ውጤታማ የምርጫ ቅስቀሳ መካሄዱን የሰልፉ አስተባባሪና የፓርቲው የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል ወ/ሪት ዘቢባ ኢብራሂም ለባልደራስ ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል አስረድተዋል፡፡

የምርጫ ቅስቀሳው ዓላማ የህብረተሰቡ አንድ አካል የሆኑት ሴቶች በቀደሙት ጊዜያት በሁሉም መልኩ የነበራቸውን የተሳትፎ ማነስ በመቃወም ሴቶች በተለያዩ መስኮች እየተሳተፉ ጥሩ ውጤት ማምጣት እንደሚችሉ ማሳያ ነው ሲሉ የቅስቀሳ ፕሮግራሙ አስተባባሪ ተናግረዋል፡፡ በተለይ ደግሞ ሴቶች በፖለካው ዘርፍ ያላቸው ሚና ከፍ ማለት እንደሚገባው፣ በተለያዩ ህጎች እና ፖሊሲዎች ላይም የሴቶች ተሳትፎ ማደግ እንዳለበት ለማሳየት እና ሴቶች ፖለቲካው ላይ መብታቸውን ለማስከበር ከኋላ ሳይሆን ከፊት ለፊት በመቀስቀስ መብታቸውን የሚያስከብሩ መሆናቸውን ወ/ሪት ዘቢባ ጨምረው ገልጸዋል፡፡

የቅስቀሳው ተሳታፊዎች ከፓርቲው ፕሬዘዳንት ከአቶ እስክንድር ነጋ ጋር በግፍ የታሠሩት የሴት ታጋይ እህቶችን የአስቴር ስዩምና የአስካለ ደምሌን ፎቶ የያዘ ከነቲራ በመልበስ እና የእነሱንም ትግል በመዘከር የፓርቲውን ዓላማ የሚገልጽ በራሪ ወረቀቶችን ለአዲስ አበባ ኗሪዎች ያደሉ መሆናቸውን የፕሮግራሙ አስተባባሪ ጠቅሰዋል፡፡ ከቀስቀሾቹ አንዷ ማህሌት እሸቱ የባልደራስ ፓርቲን እና የሴቶችን አቅም የሚያሳዩ የተለያዩ መልክቶችን በድምጽ ማጉያ አስተላልፈዋል፡፡ በሴቶች ብቻ የተካሄደው የዕለቱ ቅስቀሳ ከሕዝቡ አድናቆትን እና አክብሮትን ያስገኘ መሆኑን ዘቢባ ኢብራሂም ጠቁመዋል፡፡

እንደአስተባባሪዋ ገለጻ የቅስቀሳ መርሃ ግብሩ ባልደራስ ለእውነተኛ ዴሞክራሲ ፓርቲ በሴቶች ተሳትፎ የሚያምን ድርጅት መሆኑን እና በተግባርም መሳተፍ መቻሉን ለማሳየት ዕድል መፍጠሩን አሳውቀዋል፡፡ በተጨማሪም ለሎች ሴቶችም ትልቅ መነሳሳትን ሊፈጥር እንደሚችል እናምናለን ብለዋል፡፡

በ6ኛው አገር አቀፍ ምርጫ የምርጫ ቅስቀሳ ላይ ከሀምሳ በላይ የሚሆኑ ሴት የሕዝብ ተወካዮች እና የአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤቶች እጩ ተመራጮች እንዲሁም ሌሎች የባልደራስ ፓርቲ ሴት አባላትና ደጋፊዎች ተገኝተዋል። በመጨረሻም ወ/ሪት ዘቢባ ኢብራሂም የዕለቱ የቅስቀሳ መርሃ ግብር የተሳካ ይሆን ዘንድ ለቀስቃሽ ሴቶች የመኳኳሃ ተሽርካሪዎችን ለአቀረቡና ሌሎችም ድጋፎችን ላደረጉ ሰዎች ታላቅ ከበሬታ ያላቸው መሆናቸውን ለዝግጅት ክፍላችን ገልጸዋል፡፡

# ተበላህ አራዳ !

## ሳሙኤል አሥራት

አዲስ አበቤ “አራዳ”ን የሚጠቀምበት ለአንድ ሰፈር አሊያም ክፍለ ከተማ አይደለም። ለአዲስ አበቤ “አራዳ” ማለት ንቁ፣ የማይታለል፣ ነገር የሚገባው፣ ስልጡን. . . እንደማለት ነው። “አራዳነት” ከአዲስ አበቤው አልፎ በመላ ኢትዮጵያውያንም ዘንድ ይዘወተራል። አራዳዎች ከእነሱ በተቃራኒ ያለውን “ፋራ” ይሉታል። ሊያታልላቸው የሚሞክረው አሳማኝ ባልሆነ መልኩ ነው። ይሁንና አዲስ አበቤ አራዳነቱን በግል ይዞ፣ እንደ አዲስ አበቤ ግን ሌሎች አራዳ ሆነው ፋራ እያደረጉት ስለመሆኑ ዘለግ ያለ አመታት ታዝበናል። በተለይ የከተሜ ስልጡን ባሕሉን እንደ ድክመት ተጠቅመው፣ “ምን ጣጣ አለው” የሚለውን ስነ ልቦናውን ተንተርሰው ያሞኙታል ተብለው የማይታሰቡ አካላት ቀልደውበታል። ግለሰሰባዊ ማንነት ላይ የሚያጠነጥነውን የፖለቲካና ማሕበራዊ አመለካከቱን አጥንተው በቡድን ተደራጅተው አጥንተው ሸውደውታል። ፋራዎች ናቸው ብሎ ሲያልፋቸው እልፍ ጥቅሙን ወስደውበታል። በጉርሻ እያታለሉ የሚወዳትን ከተማውን ለመውሰድ ስልት ዘይደውበታል። የሚደግፈውን ክለቡን የደገፉ መስለው ከተማውን ሊነጥቁት ብዙ ሥራ ሰርተዋል። ለአመታት ቆጥቦ የተሠራ ቤቱን ማንም ቁልፍ ሰብሮ እንዲገባ አድርገዋል። አዲስ አበቤን ለማታለል ብዙ ተግባራት ተከውነዋል። ሰሞኑን አንድ መቀመጫውን ደቡብ አፍሪካ ያደረገ የሪልስቴት ድርጅት ከአዲስ አበባ መስተዳድር ጋር መዋዋሉ ዜና ሆኗል። ይህ ድርጅት በአምስት አመት አምስት መቶ ሺህ ቤቶችን ሰርቸ አስረክባለሁ ብሏል። ይህ ሳያንስ 4 ነጥብ 2 የአሜሪካን ዶላር ወጭ የተገመተውን የግንባታውን ወጭ ራሱ ይችላል ብለዋል።የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባለፉት 16 አመታት 200 ሺህ የጋራ መኖርያ ቤቶችን እንዳስገነባ መረጃዎች ያመለክታሉ። ለአምስት አመት ላሰራው ነው የሚለው ለ16 አመታት ከተሰሩት ቤቶች በሶስት መቶ ሺህ ቤቶች ይልቃል። ይህም ሳያንስ ከተማ አስተዳደሩ በሌሎች ባለሀብቶች በኩል ተጨማሪ ቤቶችን አስገንብቸ በአጠቃላይ በአምስት አመታት ውስጥ አዲስ አበባ አንድ ሚሊዮን ቤቶች እንዲኖራት አደርጋለሁ ብሏል። አዲስ አበባ አጠቃላይ ሕዝቧ እስከ 6 ሚሊዮን ቢሆን ነው። በአባውራ ሲሆን አጠቃላይ ቤቶች ከሁለት ሚሊዮን አይበልጡም። ይሁንና አዲስ አበባ ከተመሰረተችበት ጊዜ ጀምሮ ለ120 አመታት ከተገነቡት ያላነሱ ቤቶችን በአምስት አመት ውስጥ እናስገነባለን እያሉ ነው።በ16 አመት 200ሺህ ቤቶችን ብቻ በተገነባባት ከተማ በአምስት አመት ግማሽ ሚልዮን (በአመት መቶ ሺህ) ቤቶችን መገንባት እችላለው ብሎ መነሳት ስላቅ ነው። ሕዝብ ማሰብና መጠየቅ አይችልም ብሎ የመናቅ ምልክት ነው። የከተማ አስተዳደሩ ከሰሞኑ በፈጸመው ስምምነት መሰረት የዛሬ አመት በዕቅዱ መሰረት 100ሺህ ቤት ማድረስ ይጠበቅበታል። በ16 ዓመት 200 ሺህ ቤቶችን ብቻ የገነባ አስተዳደር በቀጣይ ጊዜ በየ ዓመቱ 100 ሺህ የመገንባት አቅም ሊያገኝ ፈጽሞ አይችልም።እነ አዳነች አቤቤ በዚህ ውል መሰረት በቀን 16 ቤት እንሰራለን ብለው ውል እንደያዙ ነው ቃል የገቡት። በኢዲስ አበባም በኢትዮጵያም ፕሮጀክቶች እንደጉድ ይጓተታሉ። ለአምስት አመት ተብሎ የተያዘ ፕሮጀክት ሁለትና ሶስት እጥፍ ጊዜ ወስዶበትም የማያልቅበት ጊዜ አለ። ዘመናዊ ቤቶች ብቻ ሳይሆን የሕዝብ ሽንት ቤት ለመስራት አመታት ይፈጅባቸዋል። እነ አዳነች ሆዬ በአንድ ቀን 16 ቤት እንሰራለን ብለው በሚዲያ ነገሩን።

የአዲስ አበባ አስተዳደር አቅም ለጊዜው እንለፈውና ይህን ፕሮጀክት ይሰራል የተባለውን ተቋም ጉዳይ ስንፈትሽ ለሚቀጥሉት አምስት አመታት 80 ሺህ ቤቶችን እሰራለሁ ያለበትን መረጃ እናገኛለን። በሀገራችን የማይመስሉ ብዙ ፕሮጀክቶች በሚዲያ ተዋውቀዋል። ባሕርዳር ላይ ይሰራል ተብሎ የነበረውን “ዋካንዳ” የተሰኘ መንደር ጉዳይ አንዘነጋውም። ይህኛውም ከዋካንዳ የተለየ አይመስልም። ኢትዮጵያ ማዕቀብ እያንጃበበባት፣ ስሟ በጦርነትና በግጭት እየተጠራ በሚገኝበት ወቅት የህዳሴ ግድቡን በጀት በራሱ ወጭ አዲስ አበባ ላይ አፈሳለሁ፣ 500 ሺህ ቤት እሰራለሁ የሚል ተቋም ተግባር እውነት ነው ብሎ አዲስ አበቤ ሊቀበል አይችልም። ከተቀበለ ደግሞ ተበላሽ አራዳ እንለዋለን።

ይህ በአምስት አመት ግማሽ ሚሊዮን ቤት እሰራለሁ ያለ ድርጅት በሌሎች አፍሪካ ሀገራት የሰራውን ደግሞ እየሰማን ነው። ብዙ ሀገራትን ቧ ቧ ሰርቷቸዋል። የፈረደበት አዲስ አበባ ሊውጣት ከቀረበው አገዛዝ በተጨማሪ ሌላም መጣበት። ተበላህ አራዳ ማለት ይሄ ነው።

# ፖሊስ በመስቀል አደባባይ ሊደረግ ታቅዶ የነበረውን መንፈሳዊ ጉባዔ ከለከለ

የአዲስ አበባ ፖሊስ በከተማዋ መስቀል አደባባይ ባለፈው ሀሙስ ሰኔ 3 ቀን 2013 ዓ.ም. ሊደረግ ታቅዶ የነበረውን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ጉባዔ ከልክሏል። ጉባዔው በአዲስ አበባ ሰንበት ትምህርት ቤቶች አንድነት ሕብረት የተዘጋጀ ሲሆን በቤተ ክርስቲያኗ አስተምህሮ መሰረት የበዓለ ዕርገት መርሐግብር የሚደረግበት ነው።

ወደ ቦታው አቅንተው በፖሊስ ክልከላ የተመለሱ ምዕመናን ድርጊቱ የአብይ አሕመድን መንግሥት አምባገነናዊነትና ጸረ ኦርቶዶክስ ተዋህዶነት ያሳየ መሆኑን ገልፀዋል። ከመካከላቸው አካላዊ ጉዳት የደረሰባቸው ያሉ ሲሆን ከፊሎቹ የጎዳና ላይ ዝማሬ እያሰሙ ተመልሰዋል። በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የወጣቶችና ጎልማሶች ማህበራት ሰብሳቢ መምህር ፋሸን ዘሪሁንን ጨምሮ አስተባባሪዎች ለሰዓታት ታስረው ተፈተዋል።

የአዲስ አበባ ፖሊስ በምዕመኑና በአስተባባሪዎቹ ላይ ርምጃ እንደሚወስድ ዝቷል። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ከደርግ ዘመነ መንግሥት መባቻ ጀምሮ ላለፉት 47 ዓመታት መንግሥታዊ ጥቃት ሲደርስባት ቆይቷል። ባለፉት ሦስት ዓመታት ደግሞ ጥቃቱ ተባብሶ ቀጥሏል፤ አብያተክርስቲያናት ተቃጥለዋል፣ ካህናት ተገድለዋል፣ ምዕመናን ፈልሰዋል።

ፖሊሲ

# የአዲስ አበባ ራስ ገዝነት እንዴት?

## (ክፍል ፩)



አመሃ ዳኘው

## ያከፋት 50 ዓመታት የአዲስ አበባ የራስ ገዝነት አስተዳደር ልምድ

በደርግ ዘመን መጀመሪያ ማለትም በ1968 ዓ.ም የአዲስ አበባ ከተማን የከተማ ቦታ ኪራይ እና የከተማ ቤት ግብር አዋጅ ለመደንገግ የደርግ መንግሥት ባወጣው አዋጅ ቁጥር 80/1968 ጋር አባሪ ተደርጎ የቀረበው የከተማዋ ካርታ ከተማዋ የትኞችን በዙሪያዋ የሚገኙ ቦታዎች እንደምታካትትና ስፋቷም 122,000 ሄክታር እንደነበር ተመልክቷል፡፡ በካርታው ውስጥ አሁን "የፊንፊኔ ዙሪያ ልዩ ዞን" በሚል የተካተቱ ቦታዎች በአዲስ አበባ የቀድሞ ይዞታ ስር እንደነበሩ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ /ካርታው ከነአዋጁ በአባሪነት ቀርቧል/ በደርግ ዘመን በ1981 ዓ.ም የራስ ገዝ አካባቢዎችን፣የአስተዳደር አካባቢዎችንና የአውራጃዎችን ለመወሰን አዋጅ ቁጥር 26/1981 በታወጀበት ጊዜ አዋጁ አዲስ አበባን በ13 የከተማ ክ/ከተሞች፣ በ20 የገጠር አውራጃዎች ከፍሏቸው ነበር፡፡ ክ/ከተማዎቹ አራዳ፣ ተክለሃይማኖት፣ አዲስ ከተማ፣ ኮልፌ፣ ጉለሌ፣ ቀጨኔ፣ እንጦጦ፣ የካ፣ ቦሌ፣ ንፋስ ስልክ፣ ቂርቆስ፣ ልደታ፣ ኮተቤ ሲሆኑ የገጠር የአዲስ አበባ አውራጃዎች ደግሞ በሰቃ፣ በረህ፣ ዓለምገና፣ ወልመራ፣ ሱልልታና አቃቂ ነበሩ፡፡ እነዚህ የአዲስ አበባ የገጠር አውራጃዎች በሥራቸው 25 ወረዳዎች ነበሯቸው፡፡ /ዝርዝሩ ከዚህ መግለጫ ጋር በአባሪነት ተያይዟል/፡፡

ከላይ እንደተጠቀሰው ከንጉሡ ዘመን ጀምሮ እስከ ደርግ ዘመን መጨረሻ ጊዜ ድረስ የአዲስ አበባ ስፋት 122,000 ሄክታር እንደነበር ልብ ይሏል፡፡ አዲስ አበባ በውሃና እህል አቅርቦት ረገድ ራሷን የቻለች ከተማ ነበረች፡፡ የገፈርሳ ውሃና በአቃቂ ዙሪያ የሚገኘው ከፍተኛ የከርሰ ምድር ውሃ በአዲስ አበባ ከተማ ይዞታ ስር ነበር፡፡ በአዲስ አበባ ይዞታ ስር በከተማዋ ዙሪያ የነበሩ በርካታ የቀበሌ የገበሬ ማህበራት ከአራቱም የኢትዮጵያ ማዕዘናት ማለትም የአማራ፣ የኦሮሞ፣ የጉራጌ እና ሌሎች የደቡብ ብሔረሰቦች ከኤርትራ ሃማሴን ሳይቀር የመጡ ሰዎች መሬት ከባለ መሬት እየተከራዩ የተለያዩ የጓሮ አትክልት እና የእህል ሰብል የሚያመርቱ ገበሬዎች የሚኖሩባቸው አካባቢዎች ነበሩ፡፡ በአጭሩ አዲስ አበባ ከመላ ኢትዮጵያ ኢትዮጵያውያን መጥተው ኑሯቸውን የሚመሰርቱበት፣ በገበሩት ግብር ያለሟት፣ የክፍለ ሃገር ኑሮ እድገታቸውን/መሻሻላቸውን እንደሚገታ ሲገምቱ ወይም በተለያዩ ችግር ምክንያት ሲፈናቀሉ የሚመጡባትና የሚጠለሉባት ከተማ ሆና የኖረች ናት፡፡

አዲስ አበባ አሁን የሚኖርባት ነዋሪ አባቶችና ቅድመ አያቶች ከየቦታው እየመጣ መኖሪያ እና መጠለያ ያደረጋት ኢትዮጵያዊ ሁሉ ነው፡፡ እስከ ህወሓት ዘመን ድረስ ኦሮሚያ የሚባል ግዛት /ክልል/ አልነበረም፡፡ በኋላ የመጣ እንጂ ቀደም ሲል በቦታው የነበረ ከኋለኛው ሊወስድ አይችልም፡፡ ሊወስድ የሚችለው በኋላ የመጣው ነው፡፡ ባለፉት 30 ዓመታት ወያኔ ከአማራው ክልል መሬት ነጥቆ ወደ ትግራይ እንደከለለው ሁሉ ህወሓት እና ኦነግ እና ኦህዴድን ለማስደሰት ሲል ቀደም ሲል በኢትዮጵያ ታሪክ የማይታወቅ ኦሮሚያ የተሰኘ ክልል ፈጠረ፡፡ ይሄ አይነት አከላለል በኢትዮጵያ የጥንትም ሆነ የመካከለኛው ዘመን የኢትዮጵያ ታሪክ የሚታወቅ አይደለም፡፡ ይሄ አዲስ ክልል ነው፡፡ ኢህአዴግ ስልጣን ከያዘ ከ1983ዓ.ም ጀምሮ የሽግግር ወቅት በመባል የሚታወቀው ከሰኔ 1983 ዓ.ም - ነሐሴ 1987 ዓ.ም በነበሩት አራት ዓመታት ውስጥ አዲስ አበባ ክልል 14 ተብላ እንደ ሌሎች የህወሐት/ኢህአዴግ ክልሎች ራሷን የቻለች ክልል እንደነበረች የሚታወቅ ነው፡፡ በህወሓት ኢህአዴግ ዘመን በተለይ ከ1997 ዓ.ም የምርጫ ሽንፈት በኋላ የአዲስ አበባ ይዞታ በየጊዜው እየጠበበ እንዲሄድ ተደርጎ ጽንፈኛ ብሔረተኞች የራሳችን ነው ወደሚሉት የኦሮሚያ ክልል እንዲካለል በማድረግ የአዲስ አበባ ይዞታ ቀደም ሲል ከነበረው እንዲቀንስ የከተማው አስተዳደርም ከከተማው ነዋሪ እጅ ወጥቶ በሞግዚት አስተዳደር ስር እንዲገባ ተደረገ፡፡

በህወሓት/ኢህአዴግ የአገዛዝ ዘመንም ቢሆን በወያኔ/ኦነግ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 49፣ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት አዲስ አበባ የፌዴራል መንግሥቱ ዋና ከተማ መሆኗ ተመልክቷል፡፡ የወያኔ/ኦነግ ህገ መንግሥትም ቢሆን በአንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 2 የአዲስ አበባ ነዋሪ ራሱን በራሱ የማስተዳደር መብት ሰጥቶታል፡፡ ከ1987 ዓ.ም እስከ 2011 ዓ.ም ድረስ የአዲስ አበባ ከተማ በየጊዜው ሲሻሻሉ የቆዩ ቻርተሮችም ቢሆኑ የከተማዋ ነዋሪ ራሱን በራሱ የማስተዳደር ሙሉ መብት እንዳለው አስረግጦ አስፍሯል፡፡ የኢፌዲሪ ህገ መንግሥት የአዲስ አበባ ነዋሪ ራሱን በራሱ ማስተደዳር ይችላል የሚል ድንጋጌ ቢኖረውም ለይስሙላ ብቻ እንደላንቲካነት ሲያገለግል በቆየባቸው ባለፉት ሃያ አምስት ዓመታት የአዲስ አበባ ሕዝብ የሃገሪቱ የፌዴራል ስርአት እንደሚደነግገው፣ ነዋሪው ራሱ በመረጣቸው ሰዎች አስተዳድሮ አያውቅም፡፡ ባለፉት 30 ዓመታት ሌሎች ክልሎች ለይስሙላም ቢሆን ከየክልላቸው በተመረጡ ሰዎች ሲመሩ አዲስ አበባና ድሬደዋ ይህ መብት እስካሁን ድረስ ተነፍጓቸው ከሌሎች ክልሎች በሚመጡ ሰዎች የሞግዚት አስተዳደር ስር እንዲወድቁ ተደርገዋል፡፡

ከላይ በቀረቡ ተጨባጭ መረጃዎች እንደተመለከተው አዲስ አበባ በዙሪያዋ ይኖሩ የነበሩ ገበሬዎች በከተማ ቀመስ የገበሬ ማህበራት ስር የታቀፉ ነበሩ፡፡ ወደ በኋላ በአዲስ አበባ ማስተር ፕላን ምክንያት ተፈናቀሉ የተባሉት ገበሬዎች ይኖሩበት የነበረው የአዲስ አበባ ዙሪያ አካባቢ ከአዲስ አበባ ተቆርጦ "የፊንፊኔ ልዩ ዞን" በሚል ከአዲስ አበባ በተወሰደ መሬት ላይ የሚኖሩ ገበሬዎች ነበሩ፡፡ እውነተኛው ክንውን የአዲስ አበባ ማስተር ፕላን የተቀየሰው ከአዲስ አበባ በተቀማው የከተማዋ መሬት ላይ እንጂ ከኦሮሚያ ክልል በተወሰደ መሬት ላይ አይደለም፡፡ ከ1997 ዓ.ም የህወሓት ሽንፈት በኋላ አቶ መለስ ዜናዊ ኦህዴድን ከናዝሬት/አዳማ ወደ አዲስ አበባ እንዲመለስ አደረገ፡፡ የአዲስ አበባ ይዞታ ቀድሞ ከነበረበት ወደ 54,000 ሄክታር እንዲጠብ ተደረገ፡፡ ከ1997 ዓ.ም በኋላ ህወሓት በአዲስ አበባ ዙሪያ ብዙ የጋራ መኖሪያ ቤቶች መሥራት ሲጀምር ከተማዋ እየተለጠጠች ከኦሮሚያ ክልል ጋር "የድንበር አለመግባባት" ችግር ተፈጠረ፡፡ የድንበር አለመግባባቱ የተፈጠረው የአዲስ አበባ የቀድሞ ይዞታ የነበረውን ህወሓት ከአዲስ አበባ ነጥቆ " የፊንፊኔ ልዩ ዞን" በሚል ወደ ኦሮሚያ እንዲካለል በማድረጉ ነው፡፡ የተፈጠረውን ችግር ለመፍታት በ2009 ዓ.ም በዶ/ር አብይ የሚመራ ኮሚቴ የአዲስ አበባን ከተማ ከኦሮሚያ እና ከአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት የተውጣጡ ባለሙያዎች እንዲያጠኑት ተደረገ፡፡ በተደረገው ጥናት በወቅቱ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር ያለው ይዞታ 54,000 ሄክታር እንደሆነ ቢገለጽም በተጨባጭ ግን የጥናቱ ውጤት ያሳየው በአዲስ አበባ አስተዳደር ስር ሆኖ የተገኘው ወደ 51,355 ሄክታር ቀንሶ ነበር፡፡ ይህም የሆነው ምንም አይነት አዋጅ ሳይደነገግ በውስጥ ለውስጥ አሠራር ነው፡፡ በአዲስ አበባ ዙሪያና በአዲስ አበባ ዙሪያ የነበሩት- እነ ሰበታ፣ ሰንዳፋ፣በኮተቤ አንቆርጫ፣ የካ አባዶ፣ የካ ጣፎ፣ ቦሌ ኮተቤ፣ ሱልልታ፣ (በበሰቃ ውስጥ አቃቂና አቃቂ ከተማ፣ ሰርቲ፣ ከዩ፣ ገላን ጎራ፣ ቂሊንጦ፣ ፈጬ፣ ቀርሳ፣ ቱሉ ሜጫ) በረህ፣ ዓለም ገና፣ ወልመራ፣ ወዘተ...ወደ ኦሮሚያ ክልል እንዲጠቃለሉ መደረጉ ይታወሳል፡፡ ከ 2009 ዓ.ም ጀምሮ የአዲስ አበባን ማስተር ፕላን ጥናት በተመለከተ የተቀሰቀሰውን ተቃውሞ ምክንያት በማድረግ በኦህዴድ ውስጥ የተነሳው ውዝግብ በእነ ድሪባ ኩማና ኩማ ደመቅሳ በኩል አዲስ አበባ በሕወሓት/ኢህአዴግ ዘመን በተለይም ከ1997ቱ ምርጫ በኋላ ሕወሓትና ኦህዴድ ተስማምተው በወሰኑላት የ54,000 ሄክታር ይዞታ መጠን ላይ መሆን አለበት ሲሉ በዶ/ር አብይና በአቶ ለማ በኩል ደግሞ የአዲስ አበባ ከተማ ይዞታ ወደ 43,000 ሄክታር ዝቅ ማለት አለበት የሚል አቋም ተያዘ፡፡ ይህ ውዝግብ መቋጫ ሳያገኝ በመጋቢት 2010 ዓ.ም ህወሓት/ኢህአዴግ ቦታውን ለኦህዴድ ለቀቀ፡፡ ኦህዴድ ውስጥ አሸናፊ ሁኖ የወጣው የጠቅላይ ሚ/ር አብይ አመራር ቀደም ሲል ባቀረበው ሃሳብ በመጽናት ከአዲስ አበባ 30 ወረዳዎች ተቀንሰው ወደ ኦሮሚያ እንዲካለሉ ይፈልጋል፡፡ ይህም ወደ ዝርዝር ሲተረጎም ከየካ ክ/ከተማ 6 ወረዳዎች፣ ከንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከተማ 1 ወረዳ፣ ከአቃቂ ክ/ከተማ 7 ወረዳዎች፣ ከጉለሌ ክ/ከተማ 5 ወረዳዎች ፣ ከቦሌ ክ/ከተማ 2 ወረዳዎች፣ ከኮልፌ ቀራኒዮ ክ/ከተማ 9 ወረዳዎች ማለት ነው፡፡ አሁን በወ/ሮ አዳነች ምክትል ከንቲባነት ዘመን ይህን ቀደም ሲል በዶ/ር ዐብይ አህመድ ሲመራ የነበረው ኮሚቴ ሲያራምድ የነበረውን 30 ወረዳዎች፣ ከአዲስ አበባ ቀንሶ ወደ ኦሮሚያ የማካለል ፍላጎት አዲስ አበባ በኦሮሚያ ክልል ሙሉ ጥገኝነት ስር እንድትወድቅ ለማድረግ ያለመ ነው፡፡ ይህ አካሄድ አዲስ አበባን በኢኮኖሚ ረገድ እንደቀድሞዋ ራሷን እንዳትችል እና ከኦሮሚያ ክልል በምታገኘው ልዩ ጥቅም ተንበርካኪ እንድትሆን የሚያደርግ አካሄድ ነው፡፡

በኦሮሞ ብልጽግና ብቻ ሳይሆን በሁሉም የኦሮሞ የፖለቲካ ድርጅቶች መካከል የተደረሰው ስምምነት አዲስ አበባ በህገ መንግሥቱ የተሰጣትን የራስ በራስ አስተዳደር በመንጠቅ ልዩ ጥቅም የሚለውን ግልጽ ያልነበረ እስካሁንም ዝርዝር ሕግ ያልወጣለት የሕገ-መንግሥት አንቀጽ ሰርዞ፣ ሙሉ ለሙሉ በኦሮሚያ ክልል ውስጥ በባለቤትነት እንድትካተት ማድረግ ነው፡፡ በፖለቲካውም ሆነ በኢኮኖሚው ረገድ በዶ/ር ዐብይ መንግሥት እየተከናወነ ያለው ተግባር በጥሞና ሲታይ ወደዚህ ግብ የሚያመራ እንደሆነ በግልጽ ይታያል፡፡ ኦህዴድ/ብልጽግና እና በኦሮሚያ ክልላዊ መስተዳድር በመደገፍ የኦሮሞ ጽንፈኛ ብሄርተኞች በአዲስ አበባ ላይ ያነሱት የባለቤትነት ጥያቄ ከታሪክ የሚቀዳ ነው የሚል ከታሪክም፣ ከሕግም፣ ከአስተዳደራዊ አወቃቀር ልምድም አንፃር ያፈነገጠ አሠራር ነው፡፡ ይህ ድርጊት ደግሞ ታሪክን በተንሸዋረረ መነጽር ከመመልከት የመነጨ አባዜ እንጂ የነሱ የባለቤትነት ጥያቄ ከተጨባጭ የታሪክ ማስረጃዎች አንፃር ውሃ የሚቋጥር ሆኖ አይደለም፡፡

በተጨባጭ ማስረጃ የሚደገፈው ታሪክ መሃል ኢትዮጵያ በኦሮሞ ጎሳዎች ከመወረሩ ከ16ኛው ክፍለ ዘመን በፊት አዲስ አበባና አካባቢዋ ብቻ ሳትሆን መላ ሸዋ የአማራ፣ የጉራጌ፣ በሂደት ወደ አማራነት የተለወጡ የሃርላ እና የጋፋት ሕዝቦች አጽመ ርስት የነበረ መሆኑ ነው፡፡ ጽንፈኛ የኦሮሞ ብሄርተኞች ይዞታ ከታሪክ ይቀዳል በሚል አካሄዳቸው "ከአጼ ምንሊክ ጀምሮ ያለው የኢትዮጵያ ታሪክ ኦሮሞ በነፍጠኛው ስርዓት በቅኝ የተገዛበት ታሪክ ነው፤ ነፍጠኛን በሰበረን ቦታ ሰብረነዋል፤ አሁን ኦሮሞ ስልጣን ከያዘ አዲስ አበባን በባለቤትነት እንጠቀልላለን" በሚል የተሳሳተ የታሪክ ትርክታቸው ከፀኑ እነሱ ሙልጭ/በዜሮ/ የሚወጡበትን አካሄድ እየተከተሉ መሆኑን ሊገነዘቡት ይገባል፡፡ የኦሮሙማ አቀንቃኝ ጽንፈኛ ብሔረተኞች ሁሉም የኛ ነው ከሚል ለከት የለሽ

አካሄዳቸው ታቅበው፣ ኢትዮጵያም ሆነች አዲስ አበባ የሁላችንም ኢትዮጵያውያን የጋራ ይዞታ መሆናቸውን ሊቀበሉ ይገባል፡፡ ከዚህ ውጭ ያለው አካሄድ የርስ በርስ ጦርነት ከመጋበዝ እና በሁሉም ላይ ጥፋት ከማስከተል ውጭ ማንም ወገን ለብቻው የሚያተርፍበት ሁኔታ ሊኖር እንደማይችል በውል ሊያስተውሉት ይገባል፡፡

እንደ ባልደራስ ለእውነተኛ ዲሞክራሲ ፓርቲ እምነት የአዲስ አበባ ጉዳይ ወደ ቀድሞው ይዞታዋ መመለስ ይኖርባታል፡፡ ይህም ማለት የይዞታ ዳር ድንበርን በተመለከተ አዲስ አበባ በንጉሡ ጊዜ እና በደርግም እስከ 1987 ዓ.ም ድረስ ወደ ነበረው የ122,000 ሄክታር ይዞታዋ መመለስ ይኖርባታል፡፡ የራስ ገዝ አስተዳደር ጉዳይንም በተመለከተ በንጉሡ ዘመን፣ በደርግ ዘመን እንዲሁም በህወሓት/ኢህአዴግ የሽግግር ወቅት ዘመን ወደ ነበረችበት የራስ ገዝ አልያም/ክልል የአስተዳደር ደረጃ ልትመለስ ይገባል፡፡ በ1987 ዓ.ም የፀደቀውና እስካሁን ያልተሻረው የኢፌድሪ ህገ መንግሥት አዲስ አበባ ከሞግዚት አስተዳደር ስር ወጥቶ ነዋሪው በነፃነት በመረጣቸው ወኪሎቹ ሊተዳደር ሲገባ፤ በአንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ተጠሪነቱ ለፌዴራል መንግሥቱ እንዲሆን ተደነገገ፡፡ የአዲስ አበባ የራስ ገዝነት ጥያቄ በታሪክም ሆነ በሕግ የተደገፈ እድሜው ከ30 ዓመት በላይ የሆነ ማንም ኢትዮጵያዊ የሚያውቀው እና የሚያስታውሰው ስለሆነ ሁሉም የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች እና የፖለቲካ ኃይሎች ሊደግፉት ይገባል፡፡ ስለዚህ በዜግነት ዙሪያም ሆነ በክልል ደረጃ የተደራጁ የፖለቲካ ድርጅቶች አዲስ አበባ ኢትዮጵያ ውስጥ ባሉ ከሰማንያ በላይ ከሆኑ ብሔረሰቦች በተውጣጡ ሕዝቦች ላብ የተገነባች መሆኗን በመረዳት እና እውነተኛ ታሪካዊ ዳራውን በማጤን እራሷን እንድታስተዳድር ሙሉ ተግባራዊ ድጋፋቸውን እንዲያበረክቱ ታሪካዊ፣ሕጋዊ እንዲሁም ሞራላዊ ኃላፊነት ወድቆባቸዋል፡፡ ስለሆነም አዲስ አበባ የመላ ኢትዮጵያ ብሔረሰቦች መገናኛ እና ማዕከል ሆና መቀጠል አለባት የሚል አቋም ያላቸው የፖለቲካ ኃይሎች/ድርጅቶች የተነሳውን የአዲስ አበባ ከተማ የተሟላ የራስ ገዝነት ጥያቄ በመደገፍ በጋራ ሊንቀሳቀሱ ይገባል ብሎ ስለሚያምን ባልደራስ ለእውነተኛ ዲሞክራሲ ፓርቲ ጥሪውን በአክብሮት ያቀርባል፡፡

# አዲስ አበባ ራሷን እንድትችል ቢደረግ የሚገኘው የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ጥቅም ምንድን ነው?

## ሀ. በፖለቲካ ረገድ

ሀ.1. እንደሚታወቀው ባለፉት ሰላሳ ዓመታት የኢትዮጵያዊነት ስሜት እና የዜግነት ፖለቲካ እንዲደበዝዝ ብሎም የጎሳ ፖለቲካ የበላይነቱን እንዲይዝ ሊደረግ የቻለው የኢትዮጵያዊነት የጠነከረ ስሜት እና የዜግነት ፖለቲካ ብቸኛ መናኸሪያ ሁኖ የተገኘችውን አዲስ አበባን የየስሙላ ፌዴራሊዝም በታወጀበት የኢፌድሪ ህገ መንግሥት እንኳ የተሰጣትን የራስ ገዝነት መብት በመከልከልና በሞግዚት አስተዳደር ውስጥ እንድትወድቅ በማድረግ ነው፡፡

ሀ.2. ቀን ተለሊት አላማቸውን ለማሳካት እየሰሩ ያሉት ጽንፈኛ የኦሮሞ ብሔረተኞች በማታለልም ሆነ በማሳመን አዲስ አበባ እውነተኛ የራስ ገዝ መብት እንዳትጎናፀፍ የማድረግ ጥረታቸው ካልተገታ የኢትዮጵያ አንድነት አደጋ ላይ የሚወድቅ ከመሆኑም በላይ የዜግነት ፖለቲካ የመጨረሻው ድንበር (The Last Frontier) ይጣሳል፡፡

ሀ.3. ኢትዮጵያ ከጎሳ ፖለቲካ ሳትላቀቅ በኢትዮጵያ ወደ ዲሞክራሲ የሚደረገው ሽግግር በምንም ተአምር ግቡን ሊመታ አይችልም፡፡ አዲስ አበባ ደግሞ የጎሳ ፖለቲካን የሚጠየፍ እና የኢትዮጵያዊነት ስሜትን የተላበሰ፣ በተጨባጭ የመላ ኢትዮጵያ ብሄረተሰቦች መናኸሪያና በ1997ቱ ምርጫ ላይ እንደታየው የዜግነት ፖለቲካ አራማጅ፣ የዘመነና ለዘመናዊ የፖለቲካ አስተሳሰብ የተጋለጠ እና የቀረበ፣ የውህድ ኢትዮጵያዊነት ብቸኛ መገለጫ ናት፡፡ ኢትዮጵያ ወደ ዲሞክራሲ የምታደርገው ሽግግር ሊጀመርና ወደ መላ ኢትዮጵያ ሊስፋፋ የሚችለው የፌዴራሊዝም ሆነ የዲሞክራሲ ውህድ አስተሳሰብ የተዋሃዳትን የአዲስ አበባ ከተማ የራስ ገዝነት መብት በተጨባጭ ማረጋገጥ ሲቻል ነው፡፡

## ለ/ በኢኮኖሚ ረገድ

ለ.1. አዲስ አበባ ከኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ከ40-50 በመቶውን የሚሆነውን ሃብት የምታመነጭ የሃገሪቱ የኢኮኖሚ ዋነኛ ሞተር የሆነች ከተማ እንደመሆኗ፣ ጽንፈኛ ብሔረተኞች ይህንን ሀብት በመቀራመት የፖለቲካ ፍላጎታቸውን ከግብ ለማድረስ በመሳሪያነት ሲጠቀሙበት ቆይተዋል፤ አሁንም እየተጠቀሙበት እንደሆነ ይስተዋላል፡፡ በቅርቡ የኦሮሞ ብልጽግና ፓርቲ የመደባቸው ም/ከንቲባ ወ/ሮ አዳነች አበቤ ከአዲስ አበባ በጀት ላይ 680 .000 /ስድስት መቶ ሰማንያ ሚሊዮን ብር / ቀንሰው ለፊንፊኔ ልዩ ዞን ተማሪዎች የደንብ ልብስ መግዣና ለምግብ አቅርቦት ማዋላቸው ለዚህ አባባል አይነተኛ ማረጋገጫ ነው፡፡

ለ.2. ኢትዮጵያ የምትመራበት የዘውግ ፖለቲካ የተቋማዊ ሙስና (Institutional Corruption) ምንጭ ነው፡፡ በኢትዮጵያ እንደ ነቀርሳ እንዲስፋፋ እየተደረገ ያለው ሙስና የአዲስ አበባ ፖለቲካን በሞግዚት የዘውግ አስተዳደር ውስጥ እንድትወድቅ በማድረግ ነው፡ ፡ እንደሚታወቀው የአዲስ አበባ የመሬት ዋጋ ከቶክዮ እና ከኒዮርክ ከተሞች የሚስተካከል ነው፡፡ በኢትዮጵያ ደግሞ የዘውግ ፖለቲካ በርካታ የፖለቲካ ደጋፊዎችን ለማፍራት የቻለው የአዲስ አበባን መሬት በመቸብቸብና ሲፈልግም ለደጋፊዎቹ ከሕግና መመሪያ ውጭ በነፃ በማደል ነው፡፡ አዲስ አበባ እውነተኛ የራስ ገዝ መብቷን እንድትጎናፀፍ ማብቃት ማለት በአንድ በኩል የዘውግ ፖለቲካን የኢኮኖሚ አቅም ማዳከም ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ የነፃ ገበያ አይነተኛ መገለጫ የሆነው የኢኮኖሚ ምህዳሩ ሁሉም ኢትዮጵያዊ በኩል የሚወዳደርበትን ሁኔታ የሚያመቻች ይሆናል፡፡ የዚህ ድምር ውጤት ደግሞ ዜጎች ፍትሃዊ የኢኮኖሚ ተጠቃሚነታቸውን እንዲያጎለብቱ ያስችላቸዋል፡፡ የአገሪቱን እድገት ሊሳለጥ የሚችለው ፖለቲካው በኢኮኖሚው ውስጥ ጣልቃ መግባቱን ሲያቆም ነው፡፡

ለ.3. ኢትዮጵያ ውስጥ ቀደም ሲል ያልነበረ ከህወሓት/ ኢህአዴግ ሥልጣን መያዝ ጋር በአዲስ የተስፋፋው ተቋማዊ ሙስና በኢኮኖሚ ተዋንያኖች መካከል የፈጠረው በሥራ ሳይሆን በአቋራጭ በሙስና የመክበር ስሜትን ፈጥሯል፡፡ በዚህም የተበላሸ አዝማሚያ ምክንያት የገበያ ሕጉ እንዲዛባና ገበያው በእውነተኛ አልሚዎች ሳይሆን በአቋራጭ በልፃጊዎች እንዲሞላ አድርጎታል፡፡ የአዲስ አበባ ራስ ገዝነት ይህንን የተበላሸ አካሄድ ከመከላከሉም ባሻገር ዜጎች ባላቸው ሙያና የትምህርት ደረጃ/ ዝግጁነት ላይ ተመስርቶ ከፍተኛ የሥራ እድል እንዲፈጠርላቸው ያስችላል፡፡

ለ.4. ባለፉት 30 ዓመታት የአዲስ አበባ ከተማ ወጣቶች አግላይ በሆነው የጎሳ ፖለቲካ በእጅጉ ሲማረሩ እንደነበር የአደባባይ ሚስጢር ነው፡፡ በመሆኑም የአዲስ አበባ የራስ ገዝነት መብት መረጋገጥ የከተማው ወጣቶችን ፍትሃዊ የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካ እንዲሁም የማህበራዊ ተጠቃሚ እንዲሆኑ የኢኮኖሚ ሜዳውን ያመቻቻል፡፡

ለ.5. የአዲስ አበባ የወደፊት ሁኔታ አጠራጣሪ በመሆኑ በሃገር አቀፍ ደረጃ ሰርቶ አገርን የማበልፀግ ስሜት በእጅጉ በመመናመኑ በኢኮኖሚው የወደፊት ሁኔታ እምነት የታጣበት (Economic Uncertainty) ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ በዚህ ምክንያት አዲስ አበባን ማዕከል ካደረገው የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ መጠኑ እጅግ ከፍተኛ የሆነ የሃገር ገንዘብ ወደ ውጭ ሃገራት እየሸሸ ይገኛል፡፡ ይህ ገንዘብ ሃገሪቱንም ሆነ አዲስ አበባን በማልማት ረገድ በከፍተኛ ደረጃ ጠቃሚ ሊሆን የሚችል ሃብት ነበር፡፡ የአዲስ አበባ ራስ ገዝ መሆን ይህን የኢኮኖሚ እምነት የማጣት እና ገንዘብን ወደ ውጭ የማሸሽ ፍላጎት ለመቅረፍ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡

ለ.6. በሃገሪቱ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የጎላ ሚና የሚጫወቱት እና በየክልሉ እየሄዱ የሚያለሙት የሃገሪቱ ባለሃብቶች የሚገኙት በአብዛኛው አዲስ አበባ ነው፡፡ በእነዚህ ባለሀብቶች አዕምሮአቸው ውስጥ የአዲስ አበባ የወደፊት እጣን በተመለከተ የጠራ ሁኔታ አለመኖሩ፣ በባለሃብቶቹ ዘንድ ኢኮኖሚ ውስጥ በሚታየው የተዛባ ፖሊሲ ሳቢያ የኢኮኖሚ ተነሳሽነታቸውን እንዲያጡ ያደርጋቸዋል፡፡ የዘውግ ፖለቲካ ውጤት የሆነው በ2012 ጥቅምት እና ሰኔ በመንጋ እርምጃ ምክንያት የደረሰው ከፍተኛ የህይወት እና የሃገር ሃብት ውድመት ባለሀብቶች ገንዘባቸውንና ተነሳሽነታቸውን በተግባር ላይ እንዳያውሉት በማድረግ የሃገሪቱን ኢንቨስትመንት በከፍተኛ ደረጃ የሚጎዳ ሆኗል፡፡ አዲስ አበባ ራሷን በራሷ ማስተዳደሯ ይህን መሰል የኢኮኖሚ እንቅፋቶችን ለመፍታት ድርሻው የጎላ ነው፡፡

## ሐ/ በማህበራዊ ዘርፍ

ሐ.1. በአዲስ አበባ እና በመላ ኢትዮጵያ ኑሮ የሚገኘው የምግብና የሸቀጣሸቀጥ ዋጋ መንግሥት ከሚከተለው የተዛባ የፋይናንስ ፖሊሲ፣ አገሪቱ ከሚያጋጥማት የእህል እጥረት ጋር የተዛመደ ቢሆንም፣ የአዲስ አበባ ቅጥ ያጣ የመሬት ዋጋ የኑሮ ውድነትን በማባባስ በኩል ከፍተኛ ሚና ይጫወታል፡፡ የአዲስ አበባን ራስ ገዝነት በማረጋገጥ የከተማው የመሬት ግብይት በሕግና በስርአት እንዲመራ በማድረግ ከፋይናንስ ፖሊሲው መስተካከል ጋር የዋጋ ንብረት እንዲቀንስና የኑሮ ውድነት ዝቅ እንዲል ያደርጋል፡፡

ሐ.2. አዲስ አበባ የቀድሞ ስፋቷ ተመልሶ በተመለሰው ይዞታዋ ላይ የራስ ገዝነት መብቷ ቢረጋገጥ፣ ከተማ ቀመስ ግብርናን በማስፋፋት ከተማዋ በእህልና በአትክልት ምርት ራሷን እንድትችል ማድረግ ስለሚቻል፣ በአዲስ አበባ የሚገኘውን በሚሊዮኖች የሚቆጠር ሥራ አጥ እና ከፊል ሥራ አጥ ሥራ በማስያዝ የሃገሪቱ ኢኮኖሚ ዋነኛ ችግር የሆነውን የሥራ አጥነት ችግር በከፍተኛ ደረጃ ለመቀነስ ይረዳል፡፡

ሐ.3. የአዲስ አበባ ራስ ገዝነት በአዲስ አበባ ውስጥ ያለውን ከፍተኛ የውሃ አቅርቦት ችግር በአዲስ አበባ ዙሪያ ያለውን ከፍተኛ የከርሰ-ምድር ውሃ በማልማት የከተማዋን በየጊዜው እየጨመረ የሚሄድን የነዋሪ ብዛት የውሃ ፍላጎት መታደግ ይቻላል፡፡

# የሌሎች የፌደራል ሃገሮች ዋና ከተሞች ተሞክሮ

በዓለም አቀፉ ደረጃ የፌዴራል ስርአትን ከሚከተሉ አገሮች ልምድ አንፃር ካየነው ለአዲስ አበባ እየተጠየቀ እንዳለው እውነተኛ የፌዴራል አስተዳደር ዋነኛ መመዘኛ የሆነው ራስን በራስ የማስተዳደር መብት እንደሆነ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

የሩሲያ ፌዴሬሽን ዋና ከተማ የሆነችው ሞስኮን ብንወስድ ሞስኮ የፌዴራል መንግሥቱ ዋና ከተማ መሆንዋ እንደተጠበቀ ሆኖ ሞስኮ ራሷን የቻለች የራስ ገዝ አስተዳደር ያላትና በበርካታ የገጠር ከተማ ቀመስ አስተዳደሮች የተዋቀረች ነች፡፡ ስያሜዋም (Greater

ወደ ገጽ 7 ዙሯል

ዳሰሳ

# ውስጠ ወይራው ያለመለወጥ <ለውጥ>

በቃሉ ሰውመሆን (የሕግ ባለሙያ)

## አቢቹ ሰብሮ የወጣው ወያኔ የጣለውን እንቁላል ነው፤

በጥቅሉ ከ 1960 ዓ.ም ወዲህ እስካለንበት በተከሰተው እንዝጭ እምቦጭ ውስጥ ኢትዮጵዊነትን ለከፍተኛ ኪሳራ የዳረገ እራስ በል እና እራስ በሉን አስቀጣይ የሆነ ሽግግራዊ ክሽፈት አጋጥሞናል፤ አንደኛው የክሽፈት አንጓ የንጉሳዊ ስርአቱን አንጸባራቂ ውርሶች አዘምኖ ማሸጋገር ሲገባ ለአውዳሚ አቢዮት መዳረጋችን ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ የኢሕአዴግን አራሙቻ ሥርዓት የሚነቅል አብዮታዊ የሥርዓት ለውጥ ማዋለድ ሲገባን ጠጋግነን ማስቀጠላችን ነው:: ቅኝ እንደተገዛ ሕዝብ ከኢትዮጵዊነት ውርስ እና ሀገር በቀል የእውቀት መሠረት ላይ ተነቅለን ተቅበዝባዥ እንድንሆን የዳረገን የፖለቲካ ታሪካችን አንዱ ዝንፈት ይህ ይመስለኛል:: አብዮት ለማይገባው አብዮት፤ አብዮት ለሚገባው ደግሞ የአስቀጣይነት ሥራ ነው የተሠራው:: በተለይ የያኔው የ60ዎቹ ትውልድ የኢትዮጵያዊ ብሔርተኛ መልካም እሴቶቻችን እና ተቋማትን ተከላክሎ እና ዘመኑን እንዲዋጅ አድርጎ ማስቀጠል ሲገባው፤ ከጭቃ እሾህ ዘውገኞች ጋር አብሮ ተሰልፎ የኢትዮጵያዊነትን ጎን መሸንቆሩ ከታሪክ ተዋቅሽነት አያድነውም:: ከመሠረታችን ተነቅለን ስናበቃ ነቃዩን አስተሳሰብ ደግሞ ለማስቀጠል ከመዋተት ያለፈ ምን እራስበልነት አለ:: መንቀል እና ማስቀጠል ያለብንን ውርሰ መሠረት ካላወቅን ዘላቂ ሥርዓት ማንበር ተስኖን ፕሮፌሰር መስፍን እንዳሉት ለእዘጭ እቦጭ ተዳርገናል:: የሥርዓት ለውጥ የሂደትም የግብም ጉዳይ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል:: ጅምሩን እና ሂደቱን ካለጎምነው ውጤቱ እንዘጭ እምቦጭ ይሆንና በለውጥ ሽፋን ተረኛ ጨቋኝ የማንበር አዙሪት ውስጥ መዳከርን ያስከትላል:: የሀገራችን ፖለቲካዊ ስነ ልቦና ትልቁ ጠባሳ ይህ ስለመሆኑ የሀሳቡ ተጋሪ ነኝ:: ለአምባገነኖች በአድርባይነት አድፍጦ መገዛት፣ ገንፍሎ መንቀል እና መልሶ አምባገነን ማንበር፤ ለዚህ አዙሪት ዋናው መንስኤው ዘለቄታዊ ሥርዓት ከማዋለድ በፊት የእርካብና መንበርን መሰላል የመጨበጥ ግለኝነት አስተሳሰብ ቀድሞ የመጋረጡ አባዜ ይመስለኛል::

ሕዝባዊ ሥርዓትን ጸንሰን ስናበቃ አገዛዝን እያዋለድን ቀጥለናል:: ከለውጥ ተብዬው ወዲህም እየሆነ ያለው ይሄው ነው:: በየትም በኩል ለውጥ ይከሰት መሠረታዊ የሥርዓት ንቅለ-ተከላ ማስፈን የመጨረሻ ግብ መሆን ነበረበት:: "በለውጡ" ዋዜማ ሕዝባዊ ትግሉ ፍሬ ሊያፈራ የሚችልበት መንታ የቢሆን ትንታኔዎች እንደ ጉም እየተነኑ ነው፤ በአንድ በኩል ሕዝባዊ ትግሉ የመንግሥትን መዋቅር ከውጭ ወደ ውስጥ የሚያጸዳ የለውጥ ምዕራፍ ላይ ደርሶ ቢሆን ኖሮ አንድም ውርሰ-ስንጥቁ አገርሽቶ የርስበርስ ሽኩቻ ሊከሰት ይችል ነበር፤ አልያም የደፈረሰው ጠርቶ ክሱት ሥርነቀል የሥርዓት ለውጥ የማዋለድ ዕድል ይፈጠር ነበር:: ሁለተኛ የሕዝቡን የለውጥ ፍላጎት ከሚጋራ የውስጥ ኃይል ጋር የተቀናጀ እና ከውስጥ ወደ ውጭ የሚፈነዳ አዝጋሚ ስር ነቀል የሽግግር ሂደት መጠንሰስ ነበር:: ይህም ለክሱት ሽግግር የሚከፈለውን ዋጋ ሊቀንሰው ይችላል:: ለለውጥ ተብዬውም ድጋፍ የተቸረው ከዚህ አኳያ ነበር:: የሆነው ግን ሕዝባዊ ትግሉ የመንግሥትን መዋቅር አጽድቶ ወደ ስርዓታዊ ሽግግር ከማምራቱ በፊት የሕዝቡን መሠረታዊ የለውጥ መሻት የሚያዋልድ መስሎ የሚያጨነግፍ አስመሳይ የውስጥ ኃይል ነው የተከሰተው:: በመሆኑም ሀገራዊ መሻትን በቡድናዊ መሻት እና ተረኛ ጨቋኝ ለሚለውጥ ቁልቁለት ተዳርገናል:: የአስቀጣዩ ዳግማዊ ኢሕአዴግ ውስጠ ወይራ አላማው ከውርሰ-መሠረቱ በአውዳሚ አብዮት የተዳፈነውን የኢትዮጵያዊ ብሔርተኝነት ከፖለቲካዊ ውክልና እንደተነቀለ አንሳፎ ማስቀረት ሲሆን፤ በአንጻሩ ደግሞ በአብዮታዊ ለውጥ መነቀል የነበረበት ኢሕአዴጋዊ ውርሰ ጥፋት በለውጥ ሽፋን አለባብሶ ማስቀጠልን ያለመ ነው:: የለውጥ ተብዬው መዘውር መንትዮሻዊ ፍላጻ ያለው ኢትዮጵያዊ ብሔርተኝነትን አዳፍኖ ማቆየት እና የዘውግ አረሙን ደግሞ አስቀጥሎ ምርቱን መሰበሰብ ነው:: በመሆኑም በተለይ ከኢትዮጵያዊ ብሔርተኛው አኳያ በለውጥ መሻቱ እና በለውጥ ሽፋን እየተሠራ ባለው ተግባር መካከል መሠረታዊ መዛነፍ፣ ተቃርኖ እና መተላለፍ ተፈጥሯል:: በኢሕአዴግ ፍጻሜ ላይ የለውጥ መሻቱ እውን መሆን ሲገባው በአንጻሩ በለወጡ ኪሳራ ኢሕአዴግን ከነጥንተ ርእዮቱ የማዳን ሥራ እየተሠራ ነው:: "የለውጥ ኃይል " ተብዬው መሠረታዊ ጭንቀት ሥርነቀል ለውጥ ከመጣ ኢትዮጵያዊ ብሔርተኝነት አብዮታዊ ውድመት (በ1960) ከማስተናገዱ በፊት ወደነበረ ልዕልናው ያንሰራራል የሚል ነው:: ሁኔታው የሚከፋው ደግሞ ኢሕአዴግ ከተፈጥሯዊ እና ከሚገባው የፖለቲካ ሞቱ እንዲያንሰራራ እየተደረገ ያለው በአዲስ ርእዮት፣ ሕገ መንግሥታዊ እና መዋቅራዊ ለውጥ ሳይሆን የነበረውን ቡቱቶ ደርቶ በማስቀጠል ነው:: እየሆነ ያለው ድራፍት እንዳይጠጣ በሀኪም ለተከለከለ ሰው ቢራ እንደማጠጣት ያክል ነው:: ታማሚው ያንኑ እየተጋተ አዲስ መድሃኒት እንደተገኘለት ያክል ይቦርቃል:: በለውጥ ሽፋን ለውጥን የመከላከል ስልት፤ ወደፊት እያዩ ወደኋላ የመራመድ የአስመሳይነት፣ የባይነት ለማለት ሳይሆን አይቀርም። እና የልግመኛነት ቁልቁለት ውስጥ ነን:: ለውጡን እናግዝ እያለ ትውልድን የሚያደናግረው የፖለቲካ አደንጓሪ በኢሕአዴግ እና በዳግማዊ ኢሕአዴግ(ብልጽግና) መካከል መሠረታዊ የርዕዮት ልዩነት ስለመኖሩ ምን ማሳያ አለው? በአመዛኙ በሂደት ይለወጣል የሚል መከራከሪያ ሲያቀርቡ ይደመጣል:: ቀድሞውንም ጥያቄው ያለው ጥንስሱ ላይ ነው እንጂ በአንድ ጀምበር ሁሉ ይከሰት የሚል አይደለም:: ዳግማዊ ኢሕአዴግ ርዕዮቱን ሳይቀይር ዘዋሪውን ብቻ ቀይሮ የተረኝነት ሀዲድ ላይ አሳፍሮን ሳለ በሂደት የሚጠበቀው ለውጥ ከተረኛ አስቀጣይነት ሊዘል ይችላል ወይ? ፖለቲካችን የሚያስፈልገው እንቁላሉን ሰብሮ የሚወጣ የውረሰ ጥፋት አስቀጣይ ሳይሆን እንቁላሉን እራሱን የሚቀይር ስርዓታዊ ለውጥ ነው:: አቢቹ ሰብሮ የወጣው ወያኔ የጣለውን እቁላል መሆኑን አንዘንጋ:: ለዚህም ነው ኢትዮጵያዊ ብሔርተኛው በራሱ ጥንተ ውርስ እና ማህበራዊ መሠረት ላይ በተባበረ ክንድ ለትግል መነሳት አለበት የምንለው:: የሆነው ሆኖ በለውጥ ሽፋን ለውጥን የመከላከል ቁልቁለቱ አያሌ ርዕዮት-ዓለማዊ፣ ተቋማዊ፣ ሕገመንግሥታዊ እና ስርዓታዊ መገለጫዎች አሉት:: እነሆ በቅንጭቡ፤

## ሀ / የ አ ዳ ፍ ኔ ነ ት እ ና አስቀጣይነት መንታ ስለት፤

የሚዳፈነው ማን ነው? የሚቀጠለውስ? የሀገራችን ፖለቲካ በተውሶ ጥብቆ መቀንበብ ከጀመረበት የተማሪዎች አብዮት ጀምሮ በተለይም ከወያኔ መከሰት ወዲህ በመሠረታዊነት በሁለት የፖለቲካ አሰላለፍ ተቃርኖ ተሰቅዟል:: የተቃርኖው ስንጥቁ በዋናነት ከላይ ከተገለጸው የሽግግር ክሽፈት አንጓ፣ ከታሪክ አረዳድ እና የነባራዊ ሁኔታ ትንታኔ ተቃርኖ ይመነጫል:: ክሱት ብያኔውም የመደብ እና የዘውግ ጭቆና ትርክት በሚለው ይሸከፋል:: በጥቅሉ የስንጥቁ አንድ መከሰቻ ከኢትዮጵዊ ውርሰ-እሴት የሚቀዳው ኢትዮጵያዊ ብሔርተኝነት/civil nationalism ሲሆን ሌላኛው የጨቋኝ ተጨቋኝ ትርክት ላይ የተጠነሰሰው የዘውግ ብሔርተኛው/ethnic nationalism ነው:: ወያኔ የተቀዳችበት ዥረት በቅኝ ገዢዎች ሀገር አፍራሽ ሴራ ተጣብቶ፣ በራስ በሉ ሌኒኒስታዊ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ታጅሎ በሻቢያ አውቆ አጥፊ ትርክት አጎንቁሎ አንቀጽ 39 ላይ የተቋተ የደም እዳ ነው:: በአመዛኙ የዘውግ ጭቆና ትርክት መሠረቱ የእውነታ ጥመት/Distortion ነው፤ በነባራዊ ሁኔታ ትንታኔ እውነትን ሳይሆን የሚበጀውን ሀሰት ፈጥሮ፣ ለነበረው እውነት አዲስ ትርጉም ሰጥቶ ለፖለቲካ ፍጆታ የማብቃት ጥመት

ነው:: ጥመት ደግሞ ከዜሮ ጀምሮ፣ በራሱ ኸረት ቀልብሶ የሚፈስ እና ሁሉን በራስ የመለወጥ ውርስ ጥፋት ነው፤ የሻቢያ፣ የወያኔ እና የኦነጋውያን ርእዮት ውርስ መሠረቱ፣ የፍሰት አቅታጫው እና መዳረሻው ስልቻ ቀልቀሎ ቀልቀሎ ስልቻ እንደሚባለው ከዚሁ የሚቀዳ ነው::

ሀገሪቱ የቆመችበትን መሠረታዊ የህላዌ ምሰሶዎችን ለጊዜያዊ የፖለቲካ ትሩፋት መሰዋት፣ ማጠልሸት፣ እንደ አዲስ መበየን፣ ከዜሮ መጀመር፣ በቅልብስ እሳቤ እና ቁልም አረዳድ የታጀለ ነው፤ የቁልቁለቱ መዳረሻ ራስ ጠልነት ነው:: የ"ብሔር ብሔረሰቦች ሕዝቦች" ምናባዊ ምስል ክሰታ፣ የተጨቋኝነት እና ቅኝ ተገዥነት ተረት፣ የአማራ ጨቋኝነት የጋራ ጠላት ምስል ክሰታ፣ እራስን በራስ... እስከመገንጠል፣ ወዘተ እውነታን እንደሚበጅ አጣሞ ለነበረው አዲስ ትርጉም መስጠት የፖለቲካ ትርፍ ማሳለጫ እና የትግል መሳሪያዎች ናቸው:: በሌኒኒስታዊ የዘውግ ጨቋኝ-ተጨቋኝ የፖለቲካ ትርክት ውስጥ ሁሉም ነገር የትግል መሳሪያ ነው:: እግዚያብሔርን ከመካድ ይነሳል፤ ታሪክ፣ ሀገር፣ ተቋማት(የሀይማኖትም ሆነ ማህበራዊ) ሰው፤ መሬት ሁሉ የፖለቲካ ትጥቅ ነው:: በትግሉ ውስጥ የሚከሰቱ ስብእናዎችም እራሳቸውን የጥቅሉ ዓለም ወይም የሀገር አንድ አካል አድርገው አይረዱም:: ይልቁኑ ሁሉም ነገር ለነሱ ሲል የሚኖር የሚመስላቸው ግላውያን/narcist ሲሆኑ እራሳቸውን ብቻ እንደግብ ያያሉ:: በዚህ ቁልቁለት ወያኔ ስንጥቁን አስምሮ ሲያበቃ ከስንጥቁ አንዱን(የጨቋኝ ተጨቋኝ ትርክትን) በዋና መሳሪያነት ተጠቅሞ የሀገሪቱን ሁለንተና እንደ ነቀዝ በልቶ ለአስቀጣዩ አስረክቦታል:: አብላጫ ማህበራዊ ቅቡልነት እያለው ከፖለቲካ ውክልና ተገፍትሮ በተንሳፋፊነት ያልበላውን እያከከ የቀጠለው ኢትዮጵያዊ ብሔርተኛው ነው::

ከዚህ አኳያ "የለውጥ ኃይል " ነኝ ባዩ አቢቹ(ኦነጋውያን) ተልእኮ እንዴት ይመዘናል? ላለፉት ሁለት ዓመታት በነባራዊ ሁኔታ ትንታኔ፣ በትርክት እና በተግባር እንደታየው እነ አቢቹ የጨቋኝ- ተጨቋኝ ትርክት ወራሾች እና አስቀጣዮች ለመሆናቸው በቂ ማሳያ አለ:: ኢትዮጵያዊ ብሔርተኛው እዚህ ላይ ብዥታ ውስጥ ገብቶ እራሱን ባያታልል መልካም ነው:: ማሳያውን ሁሉ መተንተን ለቀባሪው እንደ ማርዳት ነው:: የመደመር መጽሐፍ አስኳል መልእክቱ የጨቋኝ ተጨቋኝ ርእዮት አስቀጣይነት ነው፣ የሽመልስ አብዲሳ ሰበርናቸው ትርክት እና አማራን እያጠፋነው ነው ድብቅ ንግግር፣ የአቢቹ የአስከሬን ዘር ቆጠራ እና ለአንድ ብሔር ብለን ሕገመንግሥት አናሻሽልም ንግግር፣ ወዘተ ውስጠ ወይራ መልእክቱ የተዳፈነውን ኢትዮጵዊ ብሔርተኝነት አዳፍኖ ማቆየት እና መራሹን የዘውግ ፖለቲካ አረም ደግሞ አስቀጥሎ ምርቱን መሰበሰብ ነው:: የአዙሪቱን አንድምታ ከለውጥ ተብዬው አኳያ በዚህ መልክ ልቀንብበው፤

1ኛ. እነ አቢቹ የፖለቲካ ውርሰ ስንጥቁን ለፖለቲካ ሚዛን ማስጠበቂያነት መጠቀማቸው አስቀጣይነት አንድ ማሳያ ነው፤ በስንጥቁ ተቃርኖ የተሰቀዙትን አሰላለፎች እንደ ጽንፈኛ በመሳል እራሳቸውን በመሀል ሰፋሪና በለዘብተኛነት አቅርበው የቅቡልነት ማሳለጫ ቢያደርጉትም እራሳቸው በስንጥቁ አንድ ጫፍ የሚሰለፉ ናቸው::

2ተኛ. ኢትዮጵያዊ ብሔርተኝነት ቀና ለማለት ሲሞክር በጽንፈኝነት ፈርጆ የማዳከም ልምድ ያላቸው መሆኑ ሌላው የአዳፍኔነት ማሳያ ነው:: በመሠረቱ ልብ ማለት የሚገባው ኢትዮጵያዊ ብሔርተኝነት የፖለቲካ ተቃርኖው ጥቅል አሰላለፍ ማሳያ እንጂ በራሱ ጽንፍ አይደለም:: ምሰሶው እንዴት ጽንፍ ይሆናል? አሜሪካዊነት ለአሜሪካውያን ጽንፍ ይሆናል ወይ? ከዚህ አኳያ እየተሠራ ያለው ሤራ ሆን ብሎ ሀሳዊ መንትዬሽ/ false dichotomy እና ሀሳዊ ንጽጽር/false equivalence በማስረጽ ምሰሶውን(ኢትዮጵያዊ ብሔርተኝነትን) ከመሀል የመገርሰስ፣ ገርስሰው ሲያበቁ መሀል መንገድ ላይ እንገናኝ በሚል ፈሊጥ ጭብጦውን ይዞ ወደምሰሶው የመንኳተት፣ ብሎም መሀሉን ለብቻ የመጠቅለል እና የመሰልቀጥ አደገኛ አካሄድ ይስተዋልበታል:: ሰዋዊው እስክንድር ነጋና ዘውገኛው ጀዋር መሀመድ በጽንፍና ጽንፍ የሚፈረጁ ናቸው ወይ? የሰማይ መሰላል የሆነችው ሰንድቅ አላማችን እና የድርጅት አርማው የኦነግ ባንዲራ በጽንፍና ጽንፍ የሚፈረጁ ናቸው ወይ? OMN እና የድሮው ESAT ወይም ያሁኑ መረጃ ቲቪ በጽንፍና ጽንፍ የሚፈረጁ ናቸው ወይ? እውን የአማራ ራስን የመከላከል ተፈጥሯዊ ብሔርተኝነት እና እራስ ጠሉ የዘውግ ብሔርተኝነት የሚነጻጸሩ ናቸውን? ይህ ሁሉ የሀሳዊ መንትዬሽ/false dichotomy እና ሀሳዊ ንጽጽር/false equivalence ሰሊጡን ከኑጉ ጋር ቀላቅሎ የመውቃት የፖለቲካ ታክቲክ ማሳለጫ:: አሁን አሁንማ እስራት፣ ግድያን እና የአስከሬን ቆጠራን በራሱ በዚሁ መነጽር በብሔር ተዋጽኦ እና ከሁለቱም ጽንፍ የማዳረስ አሰራር እየተለመደ ነው:: ሁኔታው ቅኝ ብንገዛ ኖሮ ይሰራብን ከነበረው ባልተናነሰ የሀገራችንንና ህብራዊ ማንነታችንን መሠረታዊ እሴቶች የማሳጣት ብሎም ለብቻ የመጠቅለል አደገኛ ውጤት ሊያስከትል የሚችል ነው::

3ኛ. በጓያ አውድማ ላይ ጤፍ መውቃት ሌላው የአዳፍኔነት እና አስቀጣይነት ማሳያ ነው፤ እነአቢቹ(ኦነጋውያን) በትርክት ደረጃ የኢትዮጵያዊ ብሔርተኝነት ማቀንቀናቸው ከፖለቲካ ስልትነት የማያልፍ፣ ግን ደግሞ ውስጠ ወይራ አንድምታ ያለው ነው፤ ኢትዮጵያዊ ብሔርተኝነት አብላጫ ማህበረሰባዊ ቅቡልነት ቢኖረውም ሕገመንግሥታዊ እና መዋቅራዊ መሠረት እንዳይቆናጠጥ በወያኔና በመሰሎቹ አውዳሚ ሥራ ተሰርቶበታል:: ይህን ከማስቀጠል አኳያ በትርክት ደረጃ ኢትዮጵያዊ ብሔርተኝነትን ማዥጎድጎድ የፖለቲካ ማህበራዊ መሠረቱን በማሳከር በጋራ እንዳይቆም ከማድረግ ባለፈ በፖለቲካ መዋቅር ደረጃ ጠብ የሚል ውጤት እንደማያስከትል እነአቢቹ ያውቁታል:: ምክንያቱም ስንኩል ማህበራዊ መሠረት ኖሮት ሳለ ሕገመንግሥታዊ እና መዋቅራዊ መሠረት ተቆናጦ ያለው በተጨባጭ የዘውግ ጨቋኝ ተጨቋኝ ትርክት በመሆኑ ነው:: መሠረት የያዘውን የዘውግ ፖለቲካ ለማስቀጠል አንዱ ስልት መሆን ያለበት ደግሞ ኢትዮጵዊ ብሔርተኛው እውነተኛና መሠረታዊ ሽግግር የሚያስከትል ለውጥ እንዳያዋልድ በመከላከል ነው:: ይኸውም ኢትዮጵያዊ ብሔርተኛውን በትርክት ሸንግሎ ወደሰገባው በመመለስ ማዳፈን ሲቻል ነው:: በለውጥ ሽፋን ለውጥን የመከላከል አዳፍኔነት እና አስቀጣይነት ይሉሀል እንዲህ ነው:: በተለይ የአቢቹን ፖለቲካዊ ትርክቶች መአከላዊ መልእክት ለመረዳት አንዱ ዘዴ ትርክቱን ገልብጦ ማንበብ ጠቃሚ ይመስለኛል:: እያሞገሰ ይቀብርሀል፣ የልብህን እየተናገረልህ በተግባር ያልነገረህን ሤራ ያጎናጽፍሀል:: የኦነጋውያን ዋና አላማ የተካደውን ኢትዮጵያዊ ብሔርተኝነት አዳፍኖ ማቆየት እና መራሹን የዘውግ ፖለቲካ አረም ደግሞ አስቀጥሎ ምርቱን ለመሰብሰብ ይቻል ዘንድ በለውጥ ካባ ለውጥን በዘላቂነት መከላከል ነው:: ቀድሞውንም ለመቀልበስ የሚበቃ የለውጥ ፍላጎት ጅምር ስላልነበረ ባለንበት ሁኔታ የውድቀት አዙሪት ቀጠለ ነው እንጂ ለውጥ ተቀለበሰ ማለት አይቻልም::

# ከ/ የውርስ አዳ ደብዳቤውን ማን ይቅደደው?

## (ክፍል ሁለት ይቀጥላል)

## ከገጽ 7 የዞረ
## የአዲስ አበባ ራስ ገዝነት . . . . .

Moscow Area) በመባል ይታወቃል::

ጥንታዊቷ በርሊንም የጀርመን የፌዴራል መንግሥት መቀመጫ ብትሆንም ከ16ቱ የጀርመን የፌዴራል ግዛቶች መካከል እንደ አንዷ ሆና የራስ ገዝ አስተዳደር መብት እንዲኖራት ተደርጓል:: ልክ አዲስ አበባ በኦሮሚያ ክልል እንደተከበበች ሁሉ በርሊንም "ብራንድንበርግ ቡንደስላንድ" ክልል የተከበበች ናት:: ይሁንና የከተማዋ ነዋሪ የራሱን ከንቲባ የሚመርጥባት እራሱን የቻለ አስተዳደር እና እንደሌሎቹ አሥራ አምስቱ የጀርመን ራስ ገዝ /ከተሞች የራሷ ግዛት ኖሯት የተዋቀረች ናት::

የአውስትራሊያ ፌዴራላዊ አገር ዋና ከተማ የሆነችው ካንቤራም የፌዴራል መንግሥቱ ዋና ከተማ እና ራሱን የቻለ (Australian Capital Territory) የሚል የግዛት መጠሪያ የተሰጣት ከተማ ናት:: በዙሪያዋ ያሉትን ከተሞች ያካተተ የራስ ገዝ አስተዳደር ስልጣን እንዲኖራት ተደርጋ የተዋቀረች ከተማ ናት::

ከነዚህ የፌዴራል አገሮች ዋና ከተማዎች ልምድ በመነሳት አዲስ አበባም በታሪክ እና በሕግ የተደገፉ የራስ ገዝነት ስልጣን የነበራት ከተማ እንደመሆኗ የቀድሞ ስፋቷን መልሶ የፌዴራል አገሮችን ዓለም አቀፍ ልምድ ባገናዘበ መልኩ፣ የራስ ገዝነት መብት ልትጎናፀፍ ይገባል:: የባልደራስ ለእውነተኛ ዲሞክራሲ ፓርቲ ይህን የአዲስ አበባ የራስ ገዝነት ጥያቄ ያንሳው እንጂ ጥያቄው ከጽንፈኛ ብሄረተኞች ውጭ በኢትዮጵያ በየትኛውም አካባቢ ያሉ የፖለቲከ ኃይሎች የሚደግፉት ጥያቄ እንደሆነ በመተማመን፣ ለጥያቄው መመለስ ከሁሉም የኢትዮጵያ የፖለቲካ ኃይሎች ጋር በጋራ ለመሥራት ዝግጁ መሆኑን ይገልፃል::

አዲስ አበባ በነዋሪዎቿ ህብረትና አንድነት እንዲሁም በቀደመ እውነቷ በጽንፈኛ የኦሮሞ ብሔረተኞች ከተጫነባት የሞግዚት አስተዳደር ነፃ ትወጣለች!

ምርጫ 2013

# አዲስ አበቤ ከባልደራስ ምን ይጠብቅ?



(ከኢንጂነየር ቢኒያም መልሳቸው)

በአገሪቷ ላይ በርካታ የብሔር ፓርቲዎችና በጣም ውስን የሆኑ የአንድነት ፓለቲካን የሚያራምዱ ፓርቲዎች እንዳሉ ይታወቃል፡፡ ከባልደራስ ለእውነተኛ ዲሞክራሲ ፓርቲ በስተቀር በሁለቱም የፓለቲካ መስመሮች ያሉ የአዲስ አበባን ጉዳይ በምንገዶኝነት ወይም በፍርሃት ቆፈን በመተብተብ እንደ ዋና የአገሪቱ ፓለቲካዊ ማጠንጠኛ በፕሮግራሞቻቸውም ይሁን በውይይቶቻቸው አላነሱም ለማለት ያስደፍራል።

ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ደፍሮ ያላነሳቸውን የአዲስ አበባን የዘመናት የግፍ ቁልሎችን ጉዳይ ለማንሳት የባልደራስ መወለድ እውን ሆኗል፡፡ ለዚህም ምክንያት ከሆኑት አበይት ጉዳዮች መካከል ዋናው የአገሪቷ የችግሮች ሁሉ መነሻ የሆነው በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉትን ግለሰቦች እንደ ህዝብ የማያውቃቸው ህገ- መንግሥት ነው፡፡ በተለይ በአዲስ አበባ ከተማ ላይ ችግር የፈጠረው አንቀፅ 49 ቁጥር 5 ነው፡፡ የተጠቀሰው አንቀጽ የሚከተለውን ይላል፡፡ ‹‹የኦሮሚያ ክልል፤ የአገልግሎት አቅርቦት ወይም የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀምንና የመሳሰሉትን ጉዳዮች በተመለከተ እንዲሁም አዲስ አበባ በኦሮሚያ ክልል መሀል የሚገኝ በመሆኑ የሚነሱ ሁለቱን የሚያስተዳድሩ አስተዳደራዊ ጉዳዮችን በተመለከተ ያለው ልዩ ጥቅም ይጠበቅለታል፡፡ ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል፡፡››

አንቀጽ 49 ቁጥር 5 አገሪቷን ወደአስጊ ቅርቃር ውስጥ ለመክተት ተብሎ የተቀመጠ ታይም ቦንብ (ጊዜውን ጠብቆ የሚፈነዳ ቦንብ) መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ በዚህ መነሻም ተረኛ ባለሥልጣናት አዲስ አበባን ለመጠቅለል የሚወስዷቸውን እርምጃዎች ለመግታት ከየአቅጣጫው የተሰባሰቡ እልፍ የከተማችን ልጆች ባልደራስን በመመሥረት ከፍተኛ ትግል በማካሄድ ላይ ይገኛሉ።

አዲስ አበባን ወደ ራስ ገዝነት ከተማ ማምጣት የሚለው ባልደራስ ለእውነተኛ ዲሞክራሲ ፓርቲ ይዞት የተነሳው ዋነኛ ሀሳብ ነው፡፡ ባልደራስ ለ6ኛ ጊዜ ለሚካሄደው አገራዊ ምርጫ አገር አቀፍና አዲስ አበባ አቀፍ የሆኑ ሳይንሳዊ ሂደቶችን የተከተለ የፓርቲ ፕሮግራም (ማኒፌስቶዎች) አዘጋጅቶ አስመርቋል።

የዚህ ጽሑፍ ዋነኛ ዓላማ ‹‹አዲስ አበቤ ከባልደራስ ምን ይጠብቅ?›› የሚል ስለሆነ ከፓርቲው ፕሮግራም የተወሰደ የማህበረሳባዊ ኢኮኖሚ ጉዳዮችን ለመቃኘት ይሞክራል።

## ነዳጅ፡ -

በዘመናዊ ኢኮኖሚ ውስጥ ኃይልና የኃይል ጉደዮች የአንድ አገር አብይ ኢኮኖሚያዊ ውጤቶች የሚመዘኑበት መሰረታዊ ቁልፍ የምጣኔ ሀብት መለኪያ ሆነው ማገልገል ከጀመሩ ብዙ ዓመታትነ አስቆጥረዋል።

አዲስ አበባም የአገሪቷን 60% ኢኮኖሚ የምታመነጭ ከተማ ነች፡፡ ከመርፌ እስከ የኢንደስትሪ ማሽነሪ ዋጋዎች፣ የዕለት ተዕለት ጉርሳችን ከሆነው ጤፍ እስከ መድሃኒት ድረስ ያሉትን ፍጆታዎች የሚወስነው ነዳጅ የሚባል የፍጆታዎች ሁሉ ዋጋ መወሰኛ ቁስ አካል ነው።

የነዳጅ ዋጋ መጨመር ኢትዮጵያ ውስጥ አሁን ያለውን ከፍተኛ የዋጋ አለመረጋጋትን እየፈጠረ ይገኛል፡፡ የእያንዳንዱ ወር መጨረሻ ቀናት በደረሱ ቁጥር በነዋሪው ዘንድ ከፍተኛ ስጋትን ከመፍጠሩም በላይ በየነዳጅ ማደያው ለቀናት የሚቆይ ከፍተኛ የነዳጅ እጥረት ማጋጠሙ እየተለመደ መጥቷል፡፡ ሁኔታው በተለይም ካለፉት ሁለት ዓመታት ጀምሮ እየባሰ የመጣ ጉዳይ ሆኗል። ይህንን ርዕስ በሌላ ጊዜ ለብቻው የምመለስበት ቢሆንም ለአሁን ግን ለነዳጅ ግዢ በሞኖፖል የግዥ ጨረታ ከማውጣት ጀምሮ አጓጉዞ እስከ ደረቅ ወደብ ማድረስ፣ በኋላም ለኩባንያዎች መሸጥን ጨምሮ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ በወርሃዊ የዋጋ ትመና ላይ እጁ ያለበት የኢትዮጵያ ነዳጅ አቅራቢ ድርጅትን በጨረፍታ አነሳዋለሁ፡፡ ድርጅቱ ከሌሎች የመንግሥት አካላት ጋር በመሆን ግልፀኝነት በጎደለው የዋጋ ትመና ምክንያት የአገራችንን ብሎም የከተማችንን የአዲስ አበባን ነዋሪ ለከፍተኛ የኑሮ ውድነት ዳርጓል፡፡ ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት ምንም ዓይነት ጥረት ሲያደርግ አለመታየቱ ድርጅቱ በከፍተኛ ድብቅ አሠራሮች መደረቱን ጠቋሚ ነው።

ባልደራስ ለእውነኛ ዲሞክራሲ ፓርቲ ለዚህ ችግር ሁነኛ የፓሊሲ አማራጭ በፕሮግራሙ ቀርጿል፡፡ ይኸውም ከግዢ እስከ ችርቻሮ ድረስ በአንድ ተቋም ሞኖፓላይዝ ተደርጎ የተያዘውን ኢንዱስትሪ ለግሉ ኢኮኖሚ መዋዕለ ነዋይ አፍሳሽ ኩባንያዎች እንዲሁም ለዓለም አቀፍ የነዳጅ አቅራቢ ኩባንያዎች ክፍት በማድረግ በአስገዳጅ የህግ ማዕቀፍ ውስጥ ለህዝብ በተመጣጣኝ ዋጋ ነዳጅ እንዲያቀርቡ የሚያስችል የፓሊሲ አማራጭ አዘጋጅቷል። ይህም በከፍተኛ የአሠራር ብልሹነት ታንቆ የሚገኘውን የነዳጅ ኢንደስትሪ ከማፍታታቱም በላይ ከፍተኛ የውጪ ምንዛሪን ይቆጥባል።

## ትራንስፓርት

ከተማችን አዲስ አበባ እንደ ስሟ አዲስ እንድትሆን ከተፈለገ ለማኅበረሰቡ እጅግ ምቹ የሆነና አቅምን ያገናዘበ የትራንስርፖት አገልግሎት ሊቀርብለት የግድ ነው። በየቀኑ እጅግ በከፍተኛ ደረጃ ከሚስተዋሉ ችግሮች አንዱ በሥራ ሰዓት መግቢያና ከሥራ መውጫ ላይ ያለው ከፍተኛ የትራንስፓርት እጥረት ነው፡፡ ይህም አጠቃላይ ነዋሪውን ለከፍተኛ እንግልት የዳረገና በገዥው መንግሥት መፍትሄ ሊበጅለት ያልቻለ ለኑሮ ሳንካ ሆኗል።

ከተማችንን በሚመጥን መልኩ የመንገድ ስፋትና ጥራትን ያላገናዘበ የመኪና ፍሰትን እና ሳይንሳዊ መፍትሄን ባልተከተለ መልኩ እየቀረበ ያለውን አገልግሎት ወደተሻለ መንገድ ለማምጣት የሚያስችል የፓሊሲ አማራጭን ባልደራስ ይዞ ቀርቧል። ለዚህም የአጭር እና የረጅም ጊዜ እቅዶችን ነድፏል፡፡ ለምሳሌም ያህል፣ የውስጥ ለውስጥ መንገዶችን መገንባት አንዱ ይሆናል፡ ፡ የመንገድ መጨናነቅን ለመቀነስም ብዙ ህዝብን ማጓጓዝ የሚችሉ ዘመናዊ መኪኖችን ከውጪ አገር በማስገባት፣ የአገልግሎት ጊዜያቸው ያበቁ መኪኖችን ከከተማው በማስወጣት ባለንብረቶቹን የዘመናዊ ህዝብ ማመላለሻ ባለቤቶች እንዲሆኑ ማድረግ ሌላው ነው፡፡ ለባለንብረቶቹም በረጅም ጊዜ የወለድ ምጣኔ ዝቅ ባለ ብድር መስጠት የሚያስችል መፍትሄ ተቀይሷል፡፡ ባልደራስ በሚወስዳቸው በእነዚህ እርምጃዎችም የከተማው ነዋሪ በዘመነች ከተማ ላይ ብዙ የጊዜ ብክነትን የሚቆጥብ ዘመናዊ የትራንስፓርት ስምሪት ተጠቃሚ ይሆናል፡፡

ደመ-ወዝ እና የደመ-ወዝ ግብር ከ33% በላይ የዋጋ ግሸበት ባጋጠማት አገር ላይ፣ ወርን ጠብቆ በሚገኝ እዚህ ግባ በማይባል ምንዳ ይቅርና ህዝብን ደም እንባ እያስለቀሱ ኪሳቸውን ላደለቡ ሙሰኞች እንኳን ኑሮው የሚቀመስ አልሆነም። ሰው ሰራሽ የሆነን የኑሮ ውድነት ከመመከቻ ዘዴዎች አንዱ ከተቻለ የዋጋ ግሸበቱ የሚቀንስበትን የፓሊሲ አማራጭ ማፈላለግ ሲሆን ካልተቻለ ግን የዋጋ ግሸበቱ ሳይጨምር ባለበት ማስቆምና መጠነኛ የደመወዝ ጭማሪ በማድረግ ኑሮን ማረጋጋት ነው። ነገር ግን ገዥው አካል ይኸን ከማስተካከል ይልቅ በየጊዜው ገንዘብ እያተመ ወደ ገበያ በመርጨት የዋጋ ግሸበቱን እንዲባባስ አድርጎታል። የወጪ ገቢ ንግድ ሚዛንን ለማስተካከል ይረዳኛል ብሎ ያሰበው የገንዘብ የመግዛት አቅምን ማሳነስ የሚል ፓሊሲ የህዝብን ኑሮ ከማንሳቀል ውጪ የፈየደው ነገር የለም።

ባልደራስ ለእንደዚህ ዓይነት መሰረታዊ የዳቦ ጥያቄ በከተማው ላይ ላሉ የመንግሥት ሆነ የግል መሥሪያ ቤት ሠራተኞች ዝቅተኛ የመቀጠሪያ ደመወዝ ምን መምሰል እንዳለበት ይወስናል፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ ከሚመለከታቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ጋር በመሆን ዝቅተኛ የገቢ ግብር የሚከፍልበትን መንገድ ለማስወሰን ይሠራል።

## የቤት ኪራይ

አዲስ አበቤ ከፍተኛ የህይወት ውጣ ውረዶች ከሚያይባቸው መሰረታዊ ጉዳዮች አንዱ ከገቢው ጋር ያልተመጣጠነ የቤት ኪራይ ክፍያ ነው። በከፍተኛ ፍጥነት እየተወነጨፈ ያለው ይህ መሰረታዊው የሰው ልጅ ፍላጎት የሆነው የመኖሪያ ቤት ችግር፣ ገዢው አካል አባባሰው እንጂ

ወደ ገጽ 11 ዞሯል

# የባልደራስ ቅድመ ምርጫ አጠቃላይ ጥናት

## 1.መግቢያ

### 1.1.የጥናቱ መሰረታዊ ሀተታ (Statement of the Problem)

እንደ "UDHR"(1948) ክፍል 3 አንቀፅ 21 ድንጋጌ መሠረት የመንግሥት ሥልጣን መሰረቱ የሕዝቡ ፈቃድ ይሆናል፤ይህ ፈቃድም በየተወሰነ ጊዜ በሚደረግ እውነተኛ ምርጫ አማካኝነት የሚካሄድ ሲሆን ምርጫም በምስጢራዊ ድምጽ አሰጣጥ ወይም መሰል ነፃ ሂደት ሁሉን አቀፍና እኩል አሳታፊ በሆነ መንገድ የሚካሄድ ይሆናል።በተመሳሳይ ሁኔታ "ICCPR" (1966)አንቀጽ 25 ድንጋጌ መሰረት እያንዳንዱ ዜጋ በዘር፣ቀለም፣ፆታ፣ቋንቋ፣ሐይማኖት፣የፖለቲካ ወይም የሌላ አመለካከት፣ብሔር፣ወይም ማሕበራዊ ዳራ፣ሐብት፣ትውልድ ወይም ሌላ አቋም" ላይ ተመስርቶ ምንም አይነት አድልዎ ሳይደረግበት እንዲሁም ምክንያታዊነት በሌላቸው አላስፈላጊ ክልከላዎች ሳቢያ "በእውነተኛ ምርጫዎች [መምረጥና መመረጥ]"ከመሳተፍ ሳይከለከል እንዲሳተፍ የሚያስችለው ዕድል ሊፈጠርለትና የመሳተፍ መብት ሊሰጠው ይገባል ይላል። የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 38 ድንጋጌ በ"UDHR" ላይ የተቀመጠውን የፍትሀዊና የነፃ ምርጫ መርሆዎች ከማካተቱም ሌላ፣ይህ መብት በሥራ ላይ ሲውልም ኢትዮጵያ ካፀደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች፣ለምሳሌ ያህል ከ"UDHR" መንፈስ ጋራ በሚጣጣም መልኩ እንዲተገበርና ትርጓሜም እንዲሰጠው ጭምር የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንገስት አንቀጽ 13 ያሳስባል።

ምንም እንኳን የኢትዮጵያ ህገ መንግስት ይህንን ቢደነግግም በሌላ በኩል ግን የምርጫ አዋጅ ቁጥር 1162/2011 እነኝህን ዓለም አቀፍ የፍትሀዊና ነፃ ምርጫ መርሆዎች የሚጥስ ሆኖ እናገኘዋለን፤ለምሳሌ ያህል በአንድ ቦታ ከአንድ በላይ የምርጫ ጣቢያ እንዳይከፈት የሚከለክለውንና በአንድ ምርጫ ጣቢያ ከ 1,500 በላይ መራጮች እንዳይመዘገቡ የሚያግደውን ድንጋጌዎች መጥቀስ ይቻላል።

ከዚህ በተጨማሪ በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ ምርጫ ጣቢያዎች ያላቸውን የስራ እንቅስቃሴ፣ የምርጫ ጣቢያዎች የስራ ሁኔታ፣ ከአለማቀፍ ነጻና ፍትሀዊ ምርጫ መመዘኛዎች እና ከአለማቀፍ የሰብአዊ እና ዲሞክራሲያዊ ድንጋጌዎች፣ ከህገ መንግስቱ እና ከምርጫ ህጉ አንፃር ያሉበትን ሁኔታ ለመገምገምና እና በምርጫ ቦርድ አዲስ የተከፈቱ 32 ንዑስ የምርጫ ጣቢያዎችን ያሉበትን ደረጃ ለመቃኘት የባልደራስ ለእውነተኛ ዲሞክራሲ ፓርቲ የቅድመ ምርጫ ሂደቱ ምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ለመመዘን በሰጠው አቅጣጫ መሰረት ጥናት ማድረግ አስፈላጊ ሁኖ ተገኝቷል፡፡

### 1.2.የጥናቱ ዋና ዓላማ

የጥናቱ አላማ የቅድመ ምርጫ ሂደቱ (pre-election process) አካል የሆኑትን ዋና ዋና ጉዳዬች ከነፃና ፍትሀዊ ምርጫ መርሆዎች አኳያ ምን ያህል ይጣጣማል የሚለውን ጉዳይ በጥናት ማረጋገጥ ሲሆን በመራጮች ምዝገባ ሂደት ያጋጠሙ ተግዳሮቶችን፣ የምርጫ ጣቢያዎች የሚገኙበት ሁኔታ፣ መገናኛ ብዙሀን አጠቃቀምን፣ የምርጫ ቅስቀሳውን ሁኔታ፣ የመራጮች መዝገብ ግምገማ ሂደት እና አጠቃላይ የቅድመ ምርጫውን ሂደት የሚዳስስ ጥናት ነው፡፡

### 1.3.የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች

የዚህ ጥናት ዝርዝር ዓላማዎች፡-

-የመገናኛ ብዙሀን አጠቃቀምን መዳሰስ፣
-የ6ኛው ሀገራዊ ምርጫ በዕጩዎች፣በመራጮች እና በአባላት ላይ ያስከተለው የደህንነት ስጋት መቃኘት፣
-በምርጫ ቅስቀሳ ላይ የታዩ ተግዳሮቶች መፈተሽ፣
-የመራጮች መዝገብ ግምገማ ሂደትን መመርመር፣
-የምርጫ ካርድ አወሳሰድን፣ የምርጫ ህጉን፣ የምርጫ ጣቢያዎችን ሁኔታ እና የምርጫ አስፈፃሚዎችን ጉዳይ በተመለከተ ያሉትን ሁነቶች መዳሰስ ናቸው፡፡

### 1.4.የጥናቱ አስፈላጊነት (Significance of the Study)

ይህ የዳሰሳ ጥናት በምርጫ ጣቢያዎች የታዩ ተግዳሮቶችን የሚዳስስ ሲሆን የጥናት ውጤቱ ለተለያዩ የባለ ድርሻ አካላት ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ የምርጫ ቦርድ፣ የተፎካካሪ ፓርቲዎች እና በስልጣን ላይ ያለው መንግስት ከጥናቱ ግኝት ሊጠቀሙ የሚችሉ ሲሆን ማህበረሰቡም፣የምርጫ ታዛቢዎችም፣የአለም አቀፍ ማህበረሰብ እና ታዛቢዎችም ከጥናቱ ውጤት የቅድመ ምርጫ ሂደቱ ያለበትን ሁኔታ ሊገነዘብ ይችላል፡፡

1.5. የጥናቱ ወሰን (Scope of the Study)

ይህ ጥናት በዋነኛነት የሚያተኩረው በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር በሚገኙ የምርጫ ጣቢያዎች ሲሆን የቅድመ ምርጫውን አጠቃላይ ሂደት(ከመገናኛ ብዙሀን አጠቃቀምን አንፃር፣በዕጩዎች፣በመራጮች እና በአባላት ደህንነት ጉዳይ፣ቅስቀሳ ላይ የታዩ ተግዳሮቶች፣የመራጮች መዝገብ ግምገማ ሂደትን፣የምርጫ ካርድ አወሳሰድን፣የምርጫ ጣቢያዎችን ሁኔታ እና የምርጫ አስፈፃሚዎችን ጉዳይን) ያካትታል፡፡

## 2.የጥናቱ የምርምር ዘዴዎች

ይህ ጥናት በዋናነት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር እና በአንዳንድ በሀገሪቱ ክልሎች በሚገኙ የምርጫ ጣቢያዎች የሚታዩ የምርጫ ምዝገባ አገልግሎት አሰጣጥ ሂደት፤ በመገናኛ ብዙሀን አጠቃቀም፣ በእጩዎች፣ በአባላትና በመራጮችን ደህንነት፣ በምርጫ ቅስቀሳ ላይ የታዩ አጠቃላይ ተግዳሮቶች ለመለየት ታስቦ የተደረገ ሳይንሳዊ ጥናት ነው፡፡ ይህ ምርምር የምርጫ ወቅታዊ ሁኔታውን ለማብራራት የሚያግዘውን የምርምር አይነት ተጠቅሟል፡፡ ጥናቱ ፌኖሜኖሎጅ የተባለውን የአይነታዊ ጥናት የተጠቀመ ሲሆን ከዚህም ውስጥ ኢምፔሪካል ፌኖሜኖሎጅ የተባለውን የአይነታዊ የጥናት ዘዴ ተጠቅሟል፡፡ ይህ የጥናት ዘዴ በጥናቱ ላይ የተሳተፉ አካላትን ተጨባጭ የቅድመ ምርጫ ልምምድን ለመመርመር ታስቦ ነው፡፡

ጥናቱ ዓይነታዊ (Qualitative) የምርምር ዘዴ የተጠቀመ ሲሆን በአዲስ አበባ ከተማ እና በአንዳንድ በሀገሪቱ የምርጫ ጣቢያዎች የምርጫ አገልግሎት አሰጣጥ ሂደት፤ በመገናኛ ብዙሀን አጠቃቀም፣ በእጩዎች፣ በአባላትና በመራጮችን ደህንነት፣ በምርጫ ቅስቀሳ ላይ የታዩ አጠቃላይ ተግዳሮቶች ለመለየት ተሞክሯል፡፡ ጥናቱ ሁለት አይነት የመረጃ ምንጮችን ማለትም ቀዳማይ የመረጃ ምንጭ (primary source) እና ካልዓይ የመረጃ ምንጭ (secondary sources) አገልግሎት ላይ አውሏል፡፡

### 2.1.የናሙና አወሳሰድ እና አመራረጥ ስልት

ይህ ምርምር ከተጠያቂዎች ግልፅ፣ ዝርዝር፣ ተጨባጭ፣ ተገቢ እና ወቅታዊ መረጃን ይፈልጋል፡፡ ጥናቱ ሁሉን አቀፍ እና ተጨባጭ መረጃ ለመሰብሰብ ከተለያዩ የምርጫ ጣቢያዎች ናሙናዎችን ወስዷል፡፡ ምንም እንኳን በአይነታዊ (Qualitative) የምርምር ዘዴ ወካይነትን ዋና አንገብጋቢ ጉዳይ ባይሆንም ጥናቱ የሁሉንም ክፍለከተሞች አደረጃጀት ያማከለ በመሆኑ ከአብዛኛዎች ክፍለ ከተሞች መረጃዎችን ወስዷል፡፡

የጥናት ቡድኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ እና ለመተንትን ከሚያዚያ 20/2013 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ግንቦት 25/2013 ዓ.ም የተጠቀመ ሲሆን መረጃዎች የተሰበሰቡት በሁሉም ክፍለ-ከተሞች ነው ፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከሚገኙ አንደ ሺ ሰባት መቶ በላይ ከሆኑ የምርጫ ጣቢያዎች መካከል የጥናት ቡድኑ ከሶስት መቶ በላይ ከሆኑ የምርጫ ጣቢያዎችን እና ከሚያዚያ 15/2013ዓ.ም. በኃላ በምርጫ ቦርድ ከተከፈቱ ሰላሳ ሁለት ንኡስ ጣቢያወችን ያካተተ ሲሆን በአጠቃላይ ከሶስት መቶ ሰላሳ በላይ የምርጫ ጣቢያዎች አካቷል፡፡

በዚህ ጥናት የተሳረፉ የማህበረሰብ ክፍሎች የተለያዩ ሲሆኑ እነርሱም የምርጫ ምዝገባ አገልግሎት ተጠቃሚዎችን፤ የምርጫ ምዝገባ ሰራተኞችን፣ የቅስቀሳ ቡድን አባላት እና አስተባባሪዎች ፣ የመገናኛ ብዙሀን አባላት፣ የፓርቲ አመራሮች እና በምርጫ ጣቢያዎች የሚገኙ የፀጥታ አካላትን (ፖሊሶች እና ጥበቃዎች) ተጠቅሟል፡፡

### 2.2.የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

ጥናቱ የቅድመ ምርጫ አገልግሎት አሰጣጥን፣ የመገናኛ ብዙሀን አጠቃቀምን፣ የእጩዎች፣ በየአባላትና የመራጮችን ደህንነትን፣ በምርጫ ቅስቀሳ ላይ የታዩ ተግዳሮቶችን፣ የምርጫ ጣቢያዎች የሚገኙበት ሁኔታን እና የመራጮችን ቅሬታዎች በተመለከተ ትክክለኛ፣ ወቅታዊ እና ታማኝ መረጃዎችን ለመሰብሰብ የሚከተሉትን የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች አገልግሎት ላይ ውለዋል፤ ተጠቅሟል፡፡

የጥናት ቡድኑ በቀጥታ በአካል በመገኘት ሁኔታዎቹን የመረመረ ሲሆን የተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን ተጠቅሟል፡፡ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ቃለ መጠየቅ፣ የተተኳሪ ቡድን ውይይትን፣ የመረጃ ምርመራ እና በምስል መረጃዎችን(ቪዲዮዎች) የተደገፈ ምልከታ ሲሆን በምርጫ ጣቢያወች ላይ የተቀመጡ ምልክቶችና ፅሁፎች በጥናቱ ትንተና ያልተካተቱ ማስረጃዎችም በአባሪነት ቀርበዋል፡፡

### 2.3. የመረጃ ትንተና ዘዴና አቀራረብ

የመረጃው ወጥነት እና ምሉዕነት በመረጃ ሰብሳቢዎች ከተረጋገጠ በኋላ ከቃለመጠይቅ፣ ከቡድን ውይይቶች እና ከምልከታ የተገኘው መረጃ ወደ ፅሁፍ ተቀይሯል፡፡ ከዚያም ፅሁፉን በተደጋጋሚ በማንበብ፤ ኮድ በማድረግ እና ዋና ዋና ጭብጦችን በመለየት ለመተንተን ተሞክሯል፡፡ በመቀጠልም ንዑሳን ጭብጦችን ከዋና ጭብጥ ስር በማደራጀት ትንታኔ የመስጠት ተግባር ተከናውኗል፡፡ የመረጃውን ትክክለኛነት ለማጠናከር በእያንዳንዱ የጥናት ጥያቄዎች ወይንም ግቦች ስር ከባለ ጉዳዬች፣ ከምርጫ አስፈፃሚዎች፣

ወደ ገጽ 11 ዞሯል

ምርጫ 2013

# ምርጫ የሌለው ምርጫ



## ነቢዩ ውብሸት

የዘንድሮው ምርጫ ከመካኼዱ በፊት፣ኹሉን አቀፍ የእርቅና መግባባት የሽግግር ጉባዔ እንዲጠራ በተለያዩ ፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ምሁራን እንዲኹም በቅርቡ በአሜሪካን መንግሥት በኩል ሲቀርቡ የነበሩት ጥሪዎችና ምክረሐሳቦች፣ በአዴፓ-ብልጽግና መራሹ መንግሥት ተቀባይነትን ሳያገኙ በመቅረታቸው፣ምርጫው በመጪው ሰኔ 14 ቀን 2013 ዓ.ም. የሚካኼድ መኾኑ እርግጥ ኾኗል። በመጭዕው ምርጫ የተለየ ውጤት በዋነኛነት የሚጠበቀው፣ ተወዳዳሪ አማራጭ ሐሳብ ያላቸው ተፎካካሪ ፓርቲዎች በሚወዳደሩበት በአማራ ክልልና በአዲስ አበባ ብቻ ነው።

## መጭው ምርጫና " ክልሎች "

በ158 የፓርላማ ወንበር የሚወከለው የኦሮሞ ሕዝብ ድምፅ፤ በቅድመ ምርጫ ስልታዊ ትግል ወይም የጋራስምምነትም ሊኾን ይችላል - ኦነግና፣ ኦፌኮን ጨምሮ ሌሎች የኦሮሞ ብሄረተኛ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ገሸሽ የተደረጉበት እንዲኹም በከተሞች አካባቢ ከፍተኛ ተፎካካሪ ሊኾኑ የሚችሉ ተለጣፊ ያልኾኑ ኢትዮጵያዊ ብሔረተኝነትን የሚያቀነቅኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች ዝር እንዳይሉ የተደረጉበት፣አዴፓ- ብልፅግና ፓርቲ እራሱን ብቸኛ ተፎካካሪ አድርጎ ያቀረበበት ነው። ይኽ በመኾኑም፣የኦሮሞ ሕዝብ፣ በመጪው ምርጫ ከኦሮሞ ብሔረተኛው አዴፓ-ብልጽግና ውጪን ለኢትዮጵያዊ ብሔረተኝነት ድምፁን ሊሰጥ የሚችልበት እድሉ፣ሙሉ ለሙሉ ተዘግቶበታል ለማለት ይቻላል። በ138 ወንበር የሚወከለውን የአማራን ክልል እንዲኹ ብንመለከት፣ ኢትዮጵያዊነቱን ከአማራነቱ አብልጦ የሚያስቀድም ሕዝብ፣በስፋት የሚኖርበት ነው። በአኹኑ ምርጫ፣ በብሔር ያልተደራጁ እውነተኛ ኢትዮጵያዊ ብሔረተኝነትን ብቻ የሚያቀነቅኑ፣የተለጣፊነት ባኽሪ ያልተጠናወታቸው የፖለቲካ ቡድኖችን በስፋት የመምረጥ እድሉ የጠበበ ቢመስልም ፣ የመላው አማራ ሕዝብ ድርጅት (መኢአድ) በታሪካዊው የ1997ቱ ምርጫ በአማራ ክልል ቅንጅትን ወክሎ ከፍተኛ ቁጥር ያለው እጩዎችን በማቅረብ የታወቀ ፓርቲ እንደመኾኑ፣ በዘንድሮውም ምርጫ፣ እጩዎች ባቀረበባቸው ውስን የምርጫ ጣቢያዎች፣ ከፍተኛ ተፎካካሪ ኾኖ እንደሚቀርብ ይገመታል። የአማራ ሕዝብ፤ በዋናነት የቀረበለት ምርጫ፣ በአማራ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ(አዴፓ-ብልፅግና)ና እንዲኹም በአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ (አብን) መካከል የሚደረገው ከፍተኛ የምርጫ ግብ ግብ የሚጠበቅበት ፉክክር ነው። የአማራ ክልል ምርጫ፣ እንደ ኦሮሞ ክልል ምርጫ ውጤቱን በርግጠኝነት ከወዲኹ መናገር የሚቻልበት አይደለም። ነገር ግን፣ አዴፓ-ብልፅግና በቀድሞው ስሙ ብአዴን፣ ከወያኔ ኢሕአዴግ ጋር ለ30 ዓመታት ግንባር ፈጥሮ የአማራን ሕዝብ ክብርና ጥቅም አሳልፎ ሲሰጥና ሲያስገዘግዝ የኖረ እንዲኹም ባለፉት ሦስት ዓመታት፣ የኦሮሙማ ፕሮጀክት በወለደው የፖለቲካ ቁማር የተነሳ፣ አማራው ላይ ያለማቋረጥ ሲደርስበት የነበረውን ግድያና ጭፍጨፋ፣በቃላት ጋጋታ ከታጨቁ ፉከራዊ መግለጫዎችን ከማውጣት ባለፈ፣የአማራውን ሕዝብ ከግድያና ጭፍጨፋ ለመታደግ የሚያስችል ተግባራዊ እርምጃ መውሰድ ያልቻለ፣ ጥርስ የሌለው አንበሳ መኾኑን ያስተዋለው ሰፊው የአማራ ሕዝብ፣ድምፁን በስፋት ይሰጠዋል ተብሎ አይጠበቅም። በሌላ በኩል፣በመጀመሪያ የአማራን ሕዝብ ክብርና ጥቅም፣ በሰላማዊ ትግል ለማስመለስና ለማስከበር ብሎም የኢትዮጵያ ሕዝብ መብት፣ጥቅምና ክብር በእኩልነት የሚከበርባት፣የታፈረችና የተከበረች አንዲት ኢትዮጵያን መልሶ ለመገንባት አሻግሮ ያለመ ፕሮግራም ቀርፆ እየታገለ ያለው፣ በወጣት ትንታግ ምሁራን የተመሠረተውና እየተመራ የሚገኘው የአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ (አብን)፣የመመረጥ እድሉ የሰፋ ነው። ይኽን ለማረጋገጥ፣የቅርብ ጊዜ ትዝታ ኾኖ ያለፈውን፣ በኦሮሞና በቤኒሻንጉል ክልል ውስጥ በሚኖሩ አማሮች ላይ እየደረሰ የነበረውን ግድያና ጭፍጨፋ እንዲኹም ከቤት ንብረት መፈናቀል በመቃወም፣ የአማራው ወጣት " በቃ!" በማለት፣ መላው የአማራ ክልል ከተሞችን አጥለቅልቆ ወደአደባባይ የወጣበትን ሰላማዊ ሰልፍ ማስታወስ በቂ ነው። ሰልፉ በአብዛኛው ወጣት የሚበዛበት ኾኖ ብልፅግና ፓርቲን አምርሮ የረገመበትና ወጣቱ ትውልድ ብልፅግናን እንደማይደግፈው በግልፅ ያሳወቀበት አጋጣሚ ነበር። ይኽ ወደ አደባባይ ሲተም የሰነበተው የአማራ ወጣት ምርጫው ዐብን እንደሚኾን ሳይታለም የተፈታ ነው። በ38 ወንበር የሚወከለውን የትግራይ ሕዝብን ይመራ የነበረው፣በወታደራዊ አቅሙ ሲመካና ሲኩራራ የነበረው ሕወሓት፣ በወታደራዊ ኃይል ተሸንፎ ከተወገደ ሰባት ወራት ያለፈው ቢኾንም፣ ትግራይ ሙሉ ሰላሟን እስከ አኹን ድረስ ያላገኘች በመኾኗ፣በትግራይ የሚደረግ ምርጫ እንደማይኖር፣ ቀደሞውኑም የታወቀ ጉዳይ ነበር። የደቡብ ኢትዮጵያን ሕዝብ፣ ስንመለከት በ123 ወንበር የሚወከል፣የብዙ ብሔረሰቦች ከምችት የሚገኝበት ክልል በመኾኑ፣ከኦሮሞና ከአማራ ክልል ከሚደረጉት ምርጫዎች በተለየ ኹኔታ የሚንፀባርቅ እንደሚኾን ይጠበቃል። ምርጫው፣ ዝርፊያና መጭበርበር የማይፈፀምበት ከኾነ፣ጥቂትም ቢኾን፣ እንደ ሕብር ኢትዮጵያ ያሉ ሕብረብሔራዊ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ ተለጣፊነትን ባህሉ ያደረገው ኢዜማን ጨምሮ፣የተወሰኑ ወንበሮችን ከብሔረተኛ ድርጅቶች እጅ የማሸነፍ እድል ሊያገኙ የሚችሉበት ኹኔታ የሰፋ ነው። ቀሪዎቹ፣ በድምሩ በ48 ወንበር የሚወከሉት የአፋር፣ ቤንሻንጉል፣ ጋምቤላ፣ ድሬዳዋ፣ ሐረሪ እና ሶማሊ የምርጫ ክልሎች፣ በአብዛኛው ለብልፅግና ተባባሪ አጋር የሚኾኑበት ኹኔታ አመዛኝነት አለው ።

## መጪው ምርጫ በዐዲስ አበባ

ዐዲስ አበባ፣ በመላው ኢትዮጵያ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ኹሉ፣ በፍቅር የሚያይዋት የአንድነታቸው ተምሳሌት የተቀመረባት፣ኢትዮጵያውያን ኹሉ የምንወዳት፣ዋና ከተማችን ናት። ይኽ እንዳለ ኾኖ፣ዐዲስ አበባን ከሌሎች የኢትዮጵያ የምርጫ ክልሎች ለየት የሚያደርጋት ነባራዊ ኹኔታዎች አሉ፡፡ ከነዚኽም ውስጥ፣ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ጉዳይ ጎልተው ሊወጡ የሚችሉ ቢኾኑም፣ምርጫን በተመለከተ ዐዲስ አበባ፣ የራሷ የኾነ በብሔርና ጎሳ ላይ ያልተመሠረተ፣ የአስተሳሰብ ጠባይ ያላት፣ኢንተርናሲዮናል ከተማ መኾኗ ነው። ላለፉት 30 ዓመታት፣ዐዲስ አበባ ላይ ተቀምጠው ኢትዮጵያን ሲመሩ የነበሩት ኃይሎች፣ከዐዲስ አበባ ሕዝብ ጋር በሐሳብ ከመዋሃድ ይልቅ፣ በብሔር ፖለቲካ ከሚገኝ ተልከሻ፣ ዘለቄታ የሌለው ጊዜያዊ ሥልጣንና ጥቅማ ጥቅም እራሳቸውን አስገብረው፣ከተማዋን ለማስገበር ሌት ተቀን ቢተጉም፣የማይኾንላቸው ኾኖ፣ ዐዲስ አበባን በቅጡ ሳይተዋወቋት፣ የአስተሳሰቧን እውነተኛ ጣእም ሳይቋደሱ፣ይዘው የመጡትን አሮጌ የዘረኝነት ሐሳብና የለቃቀሙትን አንዳንድ ቁሳቁስ ሸክፈው፣ ወደመጡባት ከተማዋን ለቀው እንዲያፈገፍጉ ተገደዋል። ይኽ የኾነበት ምክንያት የዐዲስ አበባ ሕዝብ፣ እንደ እነዚኽ ዓይነት ባሉ፣ የጎሳ አስተሳሰብ ልክፍት ክፉኛ የተፀናወታቸውና የማይለቃቸው ኃይሎች አስተሳሰብ ተፅእኖ ሥር ሊወድቅ የሚችል ስብእና ያለው ሕዝብ ባለመኾኑ ነው። እነዚኽ እድለቢስ የጎሳ ፖለቲከኞች፣ከዐዲስ አበባ ሕዝብ ንቃተ ህሊናና የላቀ አስተሳሰብ ትምህርት ቢቀስሙ ኖሮ፣አኹን የገቡበት የውርደት ማቅ ውስጥ ባልገቡ ነበር። ኢትዮጵያም፣ አኹን ከተዘፈቀችበት የፖለቲካ ማህበራዊና የኢኮኖሚ ማጥ ውስጥ ባልተገኘች ነበር። አኹን ወዳለንበት የኢትዮጵያ ኹኔታ ስንመለስ፣በመጪው ምርጫ፣ ዐዲስ አበባ ላይ የዐዲስ አበባ ሕዝብ፣ ማንን ይመርጣል? የሚለውን ጥያቄ ስንጠይቅ፣መልሱ የብዙሀኑን የዐዲስ አበባን ሕዝብ ስብእናና ፍላጎት የተረዳ፣ ለእውነተኛ የፍትሕ ሥርዓት መስፈን፣ ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፈጣን እድገት

እንዲኹም እውነተኛ ዲሞክራሲ እንዲሰፍን፣ ተረኞችን በፅናት የታገለውን፤ በሕዝብ ዘንድ ተአማኒነትን ያተረፈውን፤ የሕዝቡን የጋለ ኢትዮጵያዊ የሀገር ፍቅር ስሜት እኩል የሚጋራውን፣ ኢትዮጵያዊ የአርበኝነትን የተላበሰውን፣ ለእውነተኛ ዲሞክራሲ የሚታገለውን፤ ከማንኛቸውም ሀገራዊም ሆነ ብሄር ተኮር፣ዐዲስ አበባ ላይ ከሚወዳደሩ የፖለቲካ ፓርቲዎች የላቀ ስእብናን ይዞ እየተጓዘ ያለውን ባልደራስ ለእውነተኛ ዲሞክራሲ ፓርቲን ነው። የዐዲስ አበባ ሕዝብ፣ ቅርሶች ሲፈርሱ በአደባባይ ቆሞ የተሟገተውን ፣ የዐዲስ አበባ ነዋሪዎቿ ከመኖሪያቸው ሲፈናቀሉና ሲገፉ ድምፅ የኾናቸውን ፣ ለዐዲስ አበባ ከተማ ህልውና አደጋ ላይ መኾን ቀድሞ ተረድቶ፣የተረኞችን ዐዲስ አበባን የመሰልቀጥ ሴራ በድፍረት የተቃወመውን ፣ አባቶቻችን ለተዋደቁላት ለእውነተኛዋ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ በአደባባይ የተሟገተውን ፣ ገዢዎችን ፊት ለፊት በመጋፈጥ የሚቃወመውን፣ በአኹኑ ሰአት፣በግፈኛ ኦዴፓ-ብልፅግና መሪዎች ትእዛዝ እስር ቤት በሚገኘው፣የዐዲስ አባባ ብርቅዬ ልጅ በኾነው በታላቁ እስክንድር ነጋ የተመሠረተውንና የሚመራውን ባልደራስን ይመርጣል። በመኾኑም፣ባልደራስ በዐዲስ አበባ የሚቀርበውን 23ቱንም የተወካዮች ምክር ቤት ወንበርና 138 የከተማዋን ምክር ቤት መቀመጫ በድምፅ የበላይነት ጠቅልሎ እንደሚያሸንፍ ይጠበቃል። ይኽን እውነታ ለመረዳት የሚቸገር ወይም መቀበል የሚከብደው ካለ፣ነፍሳቸውን ይማርና ሟቹ ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማሪያም የኢትዮጵያውያን ሕዝብ ጠባይ በአንድ መጽሐፋቸው ሲገልጡ "የኢትዮጵያ ህዝብ አድፋጭ ነው!" ያሉትን አስታውሶ፣የሐሳቡን ምንነት ለመረዳት መጣር ይኖርበታል። የዐዲስ አበባ ሕዝብ፣ በርግጥም ከምርጫ 97 በኋላ ለኹለተኛ ጊዜ፣በተረኝነት ስሜት ስነልቦናውን የማይመጥን፣የዘረኝነት አስተዳደር እያሰፈኑበት የሚገኙትን፣ኦዴፓ መራሽ ብፅግና መንግሥት እንዲኹም በወላዋይነት እድሜያቸውን የጨረሱ፣መላላክ የማይሰለቻቸው፣ የፖለቲካ ኃይሎችን በሙሉ በሠላማዊው ምርጫ መድረክ በካርዱ ሊያነጋግራቸው አድፍጦ እየተጠባበቀ ይገኛል። ለዐዲስ አበባ ሕዝብ፣ምርጫው፣ከባልደራስ ውጪ "ምርጫ የሌለው ምርጫ!" ነው። የዘንድሮው 125ኛው የአድዋ ድል በዓል በተከበረበት ጊዜ፣ ከአራዳ ጊዮርጊስ የዳግማዊ ምኒልክ አደባባይ እስከ ካዛንችዝ አድዋ ድልድይ ድረስ፣ ያባቶቹን ሰንደቅ ዓላማ በእጁ እንዳይይዝ፣ በገዢው ኦዴፓ-ብልፅግና በሚታዘዘው ፖሊስ መአቀብ ቢጣልበትም፣ ማዕቀቡን ጥሶ፣የሀገሩን ሰንደቅ ዓላማ፣በዐዲስ አበባ አውራ ጎዳናዎች ላይ "ይሔ ነው ባንዲራው! ምኒሊክ የያዘው!!" እያለ ሲያውለበልብ የዋለው የዐዲስ አበባ ነዋሪ ሕዝብ ፣ባልደራስን ይመርጣል። "ቢመችሽም ባይመችሽም፤ ሸገር ፊንፊኔ አይኾንልሽም!!" እያለ፣ለከተማው ዐዲስ አበባ የዘመረላትና ለተረኞች ምላሽ የሰጠው የዐዲስ አበባ ስታዲየም ታዳሚ፣ ባልደራስን ይመርጣል። በአጠቃላይ፣ ሀገሩን የሚወደው የዐዲስ አበባ ሕዝብ፣ከምሁር ደራሲ ከሐኪም የታሪክ ሰው ጀምሮ እስከ ጨዋ፣ ነጋዴ፣የመንግሥት ሠራተኛ ድረስ፣ባልደራስን ይመርጣል። ባልደራስ በእጩነት ያቀረባቸው እጩዎች የትምህርት ደረጃ፣ የሥራ ልምድና የሞያ ብቃት አመርቂ መኾኑን ጨምሮ፣ በሀገር ደረጃና በዐዲስ አበባ ደረጃ ያዘጋጃቸው ማኒፌስቶዎች ጥራትና ስፋት፣ሌሎች ተወዳዳሪ ፓርቲዎች ካቀረቧቸው የላቀ ኾኖ እናገኘዋለን። ምርጫው፣ በጣት የሚቆጠሩ ቀናት እየቀሩት ባለበትና ባልደራስ ለእውነተኛ ዲሞክራሲ ፓርቲ ከምርጫ ጋር የተያያዙ ደባዎችን እያጋለጠ በሚገኝበት በአኹኑ ወቅት፣የባልደራስ እጩ ተወዳዳሪዎችን ምስል የያዙ እንዲኹም የእስክንድር ነጋ ፎቶ የታተመባቸውን የባልደራስ ፖስተሮች፣በየቦታው፣ከሌሎች የጥቁር ሰማያዊ ብልፅግናና አጋራቸው እጅ አጣማሪዎቹ ኢዜማ ባነሮች ተነጥለው መቀደድ መጀመራቸውን ስንመለከት፤ ባልዳረስን በሰላማዊ ምርጫ ተፎካክረው ማሸነፍ እንደማይችሉ ከወዲኹ ተረድተው እየወሰዱት ያሉት አስፀያፊ እርምጃ መኾኑን የሚያሳይ ነው። መሬት ላይ ያለው ሐቅ፣ የባልደራስን አሸናፊ ኾኖ መውጣት የሚጠቁመን፣ብዙ መረጃዎች ያሉበት ሲኾን፣ ለመጥቀስ ያክል በምርጫ ቅስቀሳ ወቅት፣ሕዝቡ ለባልደራስ ተቀንቀሳቃሽ የቅስቀሳ ቡድን አባላት የሚሰጠው ስሜት የተሞላበትን ድጋፍ ላየ ተመልካች ኹሉ ባልደራስ፣በዐዲስ አበባ ሕዝብ ልብ ውስጥ የገባ ፓርቲ መኾኑን ለመረዳት አይከብደውም። በሌላ በኩል፣ ባለፈው ወር ዘሀበሻ (Zehabesha) https://t.me/Zehabeshanews/1444) የመረጃ አውታር፣ በቴሌግራም ቻናሉ በሠራው ከ11,500 ሰው በላይ ድምፅ በሰጠበት "የአዲስ አበባን ምርጫ ማን ያሸንፋል?" የሚል የሕዝብ አስተያየት ቅኝት(-Survey)፣ባልደራስ፣ብልፅግናንም ኾነ ተደጋፊ ተጣማጁን ኢዜማን በሰፊ ልዩነት አስከንድቶ እንዳሸነፋቸው ስናይ፣ መሬት ላይ ያለውን ኹኔታ በርግጠኝነት ለመገመት ያስችለናል። ቢኾንም፣የምርጫ ጉዳይ፣ብዙ ጣጣ ያለበት በመኾኑ፣ ባልደራስ የሚያገኘውን የሕዝብ ድምጽ የማስጠበቅ አቅሙን፣ከወዲኹ አደራጅቶ መጠበቅ ይኖርበታል። ለዚኽም፣ ሕዝቡንበተለይም ወጣቱን በንቃት በምርጫ ታዛቢነት እንዲሳተፍ መጋበዝና ማሰማራት ይኖርበታል። ጆሴፍ ስታሊን ("It's not the people who vote that count. It's the people who count the votes." ) አለ እንደተባለው፣"የምርጫን ውጤት የሚወስነው፣መራጩ ሳይኾን የመራጩን ድምፅ የሚቆጥረው ነው" እንዳለው ነውና የድምፅ ቆጠራው ላይ፣ የዐዲስ አበባ ሕዝብ፣ አጥብቆ መስራት ያለበት ብርቱ ጉዳይ ነው።

ከገጽ 8 የዞረ

## አዲስ አበቤ ከባልደራስ. . . .

ሊመልሰው አልቻለም፡፡ ለዚህም ማስረጃ የሚሆነው ለ14 ዓመታት ነዋሪዎች ከልጆቹ ጉሮሮ ላይ በመንጠቅ ገንዘብ በባንክ አጠራቅመው ‹‹ቤት እናገኛለን›› ቢሉም በተረኛ አክራሪ የዘር ጽንፈኞች ከዓይን እርግብግቢት በፈጠነ ሁኔታ ቤቶቹ ተሰልቅጠው እንቁልልጮ መባላቸው የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው።

የመኖሪያ ቤት ችግሮችን ለማቃለል ባልደራስ ለእውነተኛ ዲሞክራሲ ፓርቲ በአምስት ዓመት ውስጥ አንድ ሚሊዮን ቤቶችን ገንብቶ ለህብረተሰቡ የማድረስ ፓሊሲ ነድፏል፡፡ ከዚህ በተጓዳኝም ለመኖሪያ ቤትም ይሁን ለንግድ ቤት ቦታን በካሬ ሜትር ኪራይ በባለሙያዎች አስተምኖ ለነዋሪው ያቀርባል። ዝርዝር የአተገባበር ህጎችንም ያወጣል።

ሌሎች ጉዳዮችን በቀጣይ የምመለስበት ይሆናል፡፡ በመጨረሻም ከተማችን አሁን ላይ ያጋጠሟት እጅግ ዘርፈ ብዙ መዋቅራዊና ህገ መንግስታዊ ችግሮች ከምን ጊዜውም በላይ በጋራ ልንመከታቸው የሚገቡ የህልውና ጉዳዮች መሆናቸውን የከተማው ነዋሪ ተገንዝቦ ነገሮችን በአንክሮ እንዲከታተላቸው ለማሳሰብ እወዳለሁ ።

ከገጽ 9 የዞረ

## የባልደራስ ቅድመ ምርጫ. . .

ከቅስቀሳ ቡድን አባላት፣ ከአካባቢው ነዋሪዎች፣ከፀጥታ ኃይሎች፣ ከምልከታ፣ የተገኙ መረጃዎች በአይነታዊ ሃተታዎች አብረው ቀርበዋል፡፡ የጥናቱን መረጃ በመጠቀም የጥናቱ ውጤቶች በተለያዩ ክፍሎች ተከፋፈለው ቀርበዋል፡፡

### 2.4. የጥናቱ ተዓማኒነት ማረጋገጫ መንገዶች

የአጥኙ ቡድኑ የሚከተሉትን የጥናቱ ተዓማኒነት እና ትክክለኛነት ማረጋገጫ መንገዶችን ተጠቅሟል፡፡ የመረጃ መሰብሰቢያ መንገዶችን እና የጥናቱን አጠቃላይ እቅድ በባለሙያ ተተችቷል፤ ዋናው ጥናት ከመጀመሩ በፊት ቅድመ ጥናት ተካሂዷል፤ በመቀጠልም ሳይንሳዊ ተቀባይነት ያላቸውን የመረጃ መሰብሰቢያ መንገዶችን በመጠቀም መረጃ ተሰብስቧል፡፡

**ተዓማኒነት፡** የጥናቱን ተዓማኒነት ለማረጋገጥ በተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የተሰበሰቡት መረጃዎች እና ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች የተገኙ መረጃዎችን በአንድ ላይ በማቀናጀት የመረጃውን ተዓማኒነት ለማረጋገጥ ጥረት ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም የመረጃ ሰብሳቢዎች የትምህርት ደረጃ ጥናቱ ከሚጠብቀው የትምህርት ደረጃ በላይ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የጥናቱ የመጀመሪያ ትንታኔ በአጥኙ ቡድኑ በጋራ ተመርምሯል፤ እንዲሁም የመጀመሪያ የጥናት ትንታኔ በአንድ የከፍተኛ ተመራማሪ እንዲገመገም ተደርጓል፡፡

(ክፍል 2 ይቀጥላል)




## ዜና
## አብን በተለያዩ ከተሞች ከሕዝብ ጋር ተወያየ

የአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ (አብን) በ6ኛው አገራዊ ምርጫ አሸናፊ ሆኖ ለመውጣትና የሕዝቡን ጥያቄዎች ለመመለስ የሚያደርገውን ሀቀኛ የሰላማዊ ትግል አጠናክሮ መቀጠሉን አስታውቋል። ንቅናቄው የዚሁ መገለጫ የሆኑ ሕዝባዊ ውይይቶችንም በተለያዩ ከተሞች እያደረገ ይገኛል።በባሕር ዳር በተደረገው ሕዝባዊ ውይይት የተገኙት የቀድሞው የአብን ፕሬዚደንት ዶ/ር ደሳለኝ ጫኔ የአብን-ባልደራስ ትብብር አዲስ አበባን ራስ ገዝ አስተዳድር ለማድረግ እየሠራ መሆኑን ገልፀዋል።

አማራው "ያልተወከልንበትን ህገ-መንግሥት በውክልናችን እንለውጠዋለን!" በሚል መሪ ሃሳብ ያደረጋቸው ውይይቶች ሰፊ ሕዝባዊ ቅቡልነት የተገኘባቸው ናቸው።

ሕዝባዊ ውይይቶች ከተደረጉባቸው ከተሞች መካከል ባሕር ዳር፣ ጎንደር፣ ወልዲያና መርሳ ይጠቀሳሉ። እነኝህ ባለፉት ስድስት ቀናት ውስጥ የተደረጉና ከፍተኛ የንቅናቄው አመራሮችና የባልደራስ ለእውነተኛ ዴሞክራሲ ፓርቲ ዕጩ ተወዳዳሪዎች የተገኙባቸው ናቸው።

በወልዲያ የአብን ሊቀመንበር አቶ በለጠ ሞላ ተገኝተው ከሕዝብ ጋር ተወያይተዋል።በተመሳሳይ በመርሳ የአብን ምክትል ሊቀ መንበር አቶ የሱፍ ኢብራሒም፣ በጎንደር የሕዝብ ግንኙነት ሓላፊው አቶ ጣሂር ሙሃመድ ታድመዋል።



የአብን የምርጫ ምልክት

በተጨማሪም በባሕር ዳር በባልደራስ አዲስ አበባን በመወከል ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ዕጩ ተመራጭ የሆኑት ዶ/ር ቴዎድሮስ ኃ/ማርያም፣ የአብን የፖለቲካ ጉዳዮች ሓላፊ አቶ ክርስቲያን ታደለ እና የአደረጃጀት ጉዳዮች ሓላፊው አቶ ጋሻው መርሻ ተገኝተዋል።

"በሁሉም ከተመሞች የተደረጉት ሕዝባዊ መድረኮች ሕዝባችን የነቃ ተሳትፎ ያደረገባቸውና ከሀቀኛው የአማራ ትግል ጎን መሆኑን በሚገባ የመሰከረበት እንዲሁም በአንድ ቆመን ከአማራና ኢትዮጵያዊነት ጠል ሥርዓት የምንወጣበት መንገድ የተቀለሰበት እንደሆነ አረጋግጠናል" ብሏል የአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ።

አብን እና ባልደራስ ፖለቲካዊ ትብብር በመፍጠር በጋራ እየሠሩ ይገኛሉ። በመሆኑም በአዲስ አበባ የሚገኙ የአብን ደጋፊዎች፣ አባላትና አመራሮች ባልደራስን እንዲመርጡ፤ አማራ 'ክልል' በተባለው የአስተዳድስ ወሰን ውስጥ እና ከአዲስ አበባ ውጭ በሚገኙ ሌሎች የኢትዮጵያ ክፍሎች የሚገኙ የባልደራስ ደጋፊዎች ደግሞ የአማራ ብሔራዊ ንቅናቄን እንደመርጡ ፖለቲካዊ ትብብሩ ያሳስባል።